ORIGINAL ARTICLE

# በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጻሕፍት መልመጃዎች የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎችና የንባብ አይነቶች ውክልና ('Representation of Reading Comprehension Sub-skills and Types in Secondary Schools Amharic Text books Exercises')

**በአገኘሁ ተስ**
**Agegnehu Tesfa**

## አጠቃሎ

*በዚህ ወረቀት ሪፖርት የተደረገው ጥናት ዋና ዓላማ በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች የቀረቡ የቅድመ ንባብ፣የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ መልመጃች(ጥያቄዎች) የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎችን ለማስተማር ያላቸውን ምጥጥን፣ ለከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎች የሚሰጡትን ትኩረትና ሁለቱ የንባብ አይነቶች (ጥልቅና ሰፊ ንባብ ) ተገቢ ወክልና ማግኘት አለማግኘታቸውን መፈተሽ ነው። የጥናቱ ንድፍ ገላጭ ሲሆን ስልቱ ገምጋሚ ነው። ለዚህም በመረጃ ምንጭነት ያገለገሉት የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች ናቸው። በእነዚህ ሰነዶች ላይ በተካሄደው ምርመራ መሰረትም በመጽሐፎቹ መልመጃዎች በቅድመ ንባብ፣ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ ተግባራት ውስጥ 425 ጥያቄች አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎችን ለማስተማር እንደተዘጋጁ ማረጋገጥ ተችሏል። እነዚህ ጥያቄዎች የሚወክሏቸውን ክሂሎች ለማጥናትም ከተመራማሪው በተጨማሪ በሦስት ባለሙያዎች /በቋንቋ መምህራን ከተዛማጅ ድርሳናት ተጨምቀው በተወሰዱ 20 የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች ስር ተመድበዋል። ከዚያም የተመደቡት ጥያቄች የሚወክሏቸው ክሂሎች በሰንጠረዦች እየቀረቡ በገላጭ ስታትሲቲክስ በተለይም በድግግሞሽና በመቶኛ ተተንትነው ተተርጉመዋል። የውጤት ትንተናውና ማብራሪያው እንዳመለከተውም በክለሳ ድርሳናት ክፍል ከተገለጹት መለኪያዎች አንጻር ሲመረመሩ አንደኛ በአንብቦ መረዳት ክሂልነት ከሚታወቁትና በ፪ኛ ደረጃ ትምህርትነት ሊቀርቡ ከሚገባቸው መካከል ተካተው የተገኙት የተወሰኑት ብቻ ናቸው። አብዛኛዎቹንና በሀገሪቱ ሥርዓተ ትምህርትና የሥርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ እንዲሁም በክለሳ ድርሳናት ክፍል በተጠቀሱት ምሁራን በጣም አስፈላጊ የሚባሉትን ንዑሳን ክሂሎች ለማዳበር የሚያግዙ ጥያቄዎች በመልመጃዎቹ ውስጥ መካተት ሳይችሉ ቀርተዋል። ይህም በመጽሐፎቹ የተሸፈኑት አንብቦ የመረዳት ክሂሎች የውክልና ደረጃ ምጥጥን ችግር ያለበት እንደሆነ /በብዙ ጥያቄዎች ሊወከሉ የሚገባቸው በውስን ጥያቄዎች፣ በአንጻሩም በመመዘኛዎቹ መሰረት በዚህ ደረጃ በውስን/ጥቂት ጥያቄዎች ሊወከሉ የሚገባቸው በብዙ ጥያቄዎች እንዲወከሉ እንደተደረገ የውጤት ትንተናው አሳይቷል። ሁለተኛውን የምርምር ጥያቄ በሚመለከትም፣ዝቅተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂሎች የሚባሉት (ለምሳሌ፣ በአሰሳ ንባብ መረጃን መፈለግ፣ ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት፣ለቃላትና ሀረጋት ዐውዳዊ ፍች መስጠት) ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል። በተቃራኒው አንብቦ የመረዳት ክሂሎችን በሚያነሱ ተዛማጅ ድርሳናትና በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲና የፖሊሲው ማስተግበሪያ ማዕቀፍ ከፍተኛ ትኩረት የተሰጣቸው ከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂሎች የሚባሉትን የዘይቤያዊ አገላለጾች ፍች ከገቡበት ዐውድ መረዳት፣በጽሑፍ ውስጥ በግልጽ ያልቀረቡ ሀሳቦችንና መረጃዎችን መረዳት(inference)፣መተንተን፣ማቀናበር፣ማዛመድና መገምገም የሚባሉት በመጽሐፎቹ ዝግጅት ችላ እንደተባሉ የጥናቱ ውጤት አመላክቷል። ሦስተኛ፣ በመማሪያ መጽሐፎቹ ጥልቅ (intensive) እና ሰፊ (extensive) የንባብ አይነቶች ያገኙት ትኩረት ሲመረመርም ሰፊ የሚባለው የንባብ አይነት ትኩረት እንዳልተሰጠው ብቻ ሳይሆን ጭራሽ እንደተዘነጋ ለማረጋገጥ ተችሏል። በአጠቃላይ በሦስቱም ጉዳዮች ላይ የተካሄደው የውጤት ትንተና የመማሪያ መጽሐፎቹ የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ጥያቄዎች አዘገጃጀት በተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ የቀረበውን የክሂሎች አቀራረብ የሚጻረር እንደሆነ አመላክቷል። ከእነዚህ የጥናቱ ግኝቶች በመነሳትም ወደፊት መጽሐፎቹ ሲሻሻሉ ሊደረጉ የሚገባቸው ጥንቃቄዎች እንዲሁም መምህራን ምን ቢያደርጉ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን የሚታዩትን ክፍተቶች ሊሞሉ እንደሚችሉ የሚያመላክቱ የመፍትሄ ሀሳቦች ተጠቁመዋል።*

## መግቢያ

በብዙ የቋንቋ ትምህርቶች ለንባብ ትምህርት፣ በተለይ ደግሞ ለአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች የተለየ ትኩረት ይሰጣል (ስፔርስ፣2006፤ኩታ፣2008፤ስቶን፣2009፤ሪቻርድስና ሬናንዲያ ፣2002)።

ለዚህም ብዙ ምክንያቶች ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ መካከል ሰዎች እያነበቡ መረጃ ለማግኘትና ለመዝናናት፣በስራ ዕድገት ለማግኘትና በትምህርት ራሳቸውን ለማሻሻል አስፈላጊነቱ፤ጥሩ የማንበብ ችሎታ ጥሩ ለመጻፍም መሰረት መሆኑ፤የቋንቋ ችሎታን ለማሻሻልም (ለምሳሌ፣ የቃላት አቅምን፣የሰዋስውና የፈሊጥ ችሎታን ለማዳበር) ማንበብና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዋነኛ ጉዳይ ሆኖ መገኘቱ የሚሉት ይገኙበታል(ሪቻርድስና ሬናንዲያ ፣2002፤ስቴርስ፣2006 እና ግሊንኮ፣1976)። በዚህም የተነሳ ማንበብ በተለይም አንብቦ የመረዳት ችሎታ በተማሪዎችም ሆነ በመምህራን ከፍተኛ ዋጋ የሚሰጠው ክሂል ሊሆን እንደቻለ የመስኩ ምሁራን (ለምሳሌ ሪቻርድስና ሬናንዲያ፣2002፤ስቴርስ፣2006፤ኩታ፣ 2008፤ ስቶን ፣2009፤ሰዩሶ-ጃንና ማርቲን ፍሎር፣2006) ይገልጻሉ። ይሁን እንጂ በኢትዮጵያ በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ለአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች የተሰጠው ትኩረት ምን ይመስላል? የሚለው ትኩረት አግኝቶ እየተጠና ያለ ጉዳይ ሆኖ አልተገኘም። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማም መሰረታዊ የሚባሉ አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎችና ጥልቅና ሰፊ ንባብ በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ መማሪያ መጻሰሕፍት ምን ያህል ትኩረት እንዳገኙና የውክልናቸው ደረጃ ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነው። አንብቦ መረዳት የሚለው የማንበብ ክሂል በውስጡ በርካታ ክሂሎች የተካተቱበት ነው። ከእነዚህ መካከል የአንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎችን በሚያነሱ መጻሕፍት ዋና ዋና ተብለው በተደጋጋሚ የሚጠቀሱት፣አንደኛ በአሰሳና ግርፍ ንባብ መረጃ መፈለግ፣ ሁለተኛ ርዕሰ ጉዳይ፣ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችንና የደራሲውን ዓላማ መለየት፣ በራስ አባባል መግለፅና ማሳጠር፣ሦስተኛ የቃላትና ሀረጋትን ዐውዳዊ ፍች መረዳት፣ አራተኛ ቃላዊና ሰዋስዋዊ አያያዞችን መረዳት፣ አምስተኛ በግልፅ ያልሰፈሩ ሀሳቦችንና መረጃዎችን አንድምታ መረዳት/መተንበይ፣የቀደመ ዕውቀትንና በፅሑፉ ውስጥ የሚገኙ ፍንጮችን መነሻ በማድረግበግልፅያልቀርቡ ሀሳቦችንና መረጃዎችን መረዳት፣የምስሎችን፣የካርቱኖችን፣የስዕሎችን፣የሰንጠረዦችን፣የካርታዎችን፣የግራፎችንና የፎቶዎችን አንድምታ መረዳት፣ ስድስተኛ፣ በዘይቤያዊ አገላለፅ የቀረቡ ሀሳቦችን መረዳት፣ ሰባተኛ መተንተን፣ ስምንተኛ ማዛመድ፣ ዘጠነኛ ማቀናበር፣አስረኛ መገምገም የሚሉት ናቸው (ኩታ ፣2008፤ ስቴርስ፣2006፤ሜዘርና ማካርቲ ፣2005)። ከእነዚህ ክሂሎች መካከል አንዳንዶች፣በአንዳንድ ምሁራን ስራዎች ብልሃቶች (strategies) እየተባሉ የሚጠሩ ቢሆንም በዚህ ጥናት ግን አንዳንድ ምሁራን እንደሚያደርጉት በክሂልነት ተመድበዋል። ከእነዚህ የአንብቦ መረዳት ክሂሎች መካከል ከተራ ቁጥር አንድ እስከ አራት የተጠቀሱት በዝቅተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂልነት የሚታወቁ ሲሆኑ ከአምስተኛ እስከ አስረኛ የቀረቡት ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂልነት የሚመደቡ ናቸው (ግርሌት፣1996፤ጁዴና አጁዬ ፣2012) ።

ኑሩ(1992)፣ኤሊስና ሌሎች(1984) በመጥቀስ ጭምር እንደገለፁት የቋንቋ ትምህርት የመማሪያ መጻሕፍት ጠንካራ ተፅዕኖ ውጤት ነው። በአማርኛ ቋንቋም በተለይ በክሂሎች ትምህርት ረገድ ያለው እውነታም ከዚህ የተለየ አይደለም። ከሚታሰበው በላይ ትምህርቱ የመማሪያ መጽሐፎቹ ጥገኛ ነው (አገኘሁ፣2005)። ይህም የመማሪያ መጽሐፎቹ ተገቢ የመማሪያ ተግባራትን ከያዙ ትምህርቱ በተሻለ ደረጃ እንዲሰጥ ሊያግዙ እንደሚችሉ ያሳያል። በሌላ በኩል ደግሞ የመማሪያ መጻሕፍቱ መልመጃዎች አዘገጃጀት በእንከን የተሞላ ከሆነ በተቃራኒው የመማር ማስተማር ሂደቱ እንዲደናቀፍ የሚያደርግ አሉታዊ ሚና መጫወቱ አይቀሬ ይሆናል። በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት በአፍ መፍቻም ሆነ በሁለተኛ ቋንቋ የተማሪዎች የቋንቋ ችሎታ በተለይም በክሂሎች ረገድ በጣም እየተዳከመ መጥቷል (ፈቃድ፣1999፤ዮናስ፣1999፤ አገኘሁ፣2005)። የዚህ ችግር አንዱ መንስኤ በተለይም አንብቦ የመረዳት ክሂል ደካማነት ከመማሪያ መጽሐፎቹ አዘገጃጀት ሊሆን ስለሚችል የመማሪያ መጻሕፍቱን የቅድመ ንባብ ፣ የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ መልመጃዎች በመመርመር ለተማሪዎች አንብቦ መረዳት ችሎታ መዳከም ድርሻ እንዳለውና እንደሌለው መረጃ ለመስጠት ነው። በሀገሪቱ የትምህርት ሥርዓት አብዛኛው ተማሪ መደበኛ ትምህርቱን እንዲያጠናቅቅ የሚጠበቀው 10ኛ ክፍል መጨረሻ ላይ ነው። በመሆኑም የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ተማሪዎች ወደ መሰናዶ ትምህርት ካላለፉ በስተቀር ከአስረኛ ክፍል በኋላ ቋንቋውን የሚማሩበት ሌላ እድል አይኖራቸውም። ስለዚህ እነዚህን መጻሕፍት ለመመርመር የተፈለገበት ሁለተኛው ምክንያት የሚጠኑትን ጉዳዮች በሚመለከት ተማሪዎች በቋንቋው ትምህርት የሚጠበቀውን አቅም ፈጥረው ትምህርታቸውን እንዲያጠናቅቁ የመማሪያ መጻሕፍቱ ምን ያህል እንደሚያግዟቸው ወይም እንደማያግዟቸው ለመፈተሽ ነው።

በዚሁ መንገድ የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂሎች አዳብረው፣ምን ያህል ለተሻለ የቋንቋ አጠቃቀም ዝግጁ ያደርጓቸዋል? የሚለው ካልተጠና፤ የመጽሐፎቹን ሚና ማወቅም ሆነ ወደ ፊት ሲሻሻሉ ሊስተካከሉ የሚገባቸውንጉዳዮች ለመለየት አይቻልም። ከዚህ አስተሳሰብ በመነሳትም የመማሪያ መጽሐፎችን መልመጃዎች/ጥያቄዎች ለመግለጽና ለመተንተን የተለያዩ የምርምር ጥያቄዎች ሊነሱ ይችላሉ። በዚህ ጥናት የ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ መማሪያ መጽሐፎችን አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች በመግለጽና በመተንተን ለመመለስ የተሞከረውም የሚከተሉትን የምርምር ጥያቄዎች ነው፤

1. የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ የአማርኛ ቋንቋ መማሪያ መጽሐፎች የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎች ተወክለውበታል?ተወክለው ከሆነስ የክሂሎች ውክልና ተመጣጣኝ ነው?
2. በመልመጃዎቹ ከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂሎች ከዝቅተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂሎች የተሻለ ውክልና አግኝተዋል?
3. በመማሪያ መጽሐፎቹ ለሁለቱ የንባብ አይነቶች(ለጥልቅና ሰፊ ንባብ) ትኩረት ተሰጥቷል?

በንባብ ላይ ትኩረት አድርገው ምርምር የሚያካሂዱና ስለአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች ጥያቄዎች አዘገጃጀት የጻፉ የቋንቋ ምሁራን (ለምሳሌ ግርሌት፣1996፤ኩታ፣2008፤ናታል፣ 1996) እንደሚገልጹት ተማሪዎችን ለተለያዩ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች፣ በተለይ ደግሞ ከፍተኛ ደረጃ ለሚባሉት ክሂሎች የሚያጋልጡ ጥያቄዎች ማካተት በጣም አስፈላጊና የተለየ ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። ይህ ጥናትም ከምንባቦቹ የወጡ ጥያቄዎችን ደረጃ (levels of questions)በመለየት አሁን እየተሰራባቸው ያሉት መማሪያ መጻሕፍት እንደሚጠበቀው የተለያዩና ከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎች ላይ ያተኮሩ መሆን አለመሆናቸውን በማሳየት ረገድ አስፈላጊነቱ ከፍተኛ ነው ተብሎ ይታመናል። የጥያቄዎቹ አዘገጃጀት ችግር የሚታይበት ሆኖ ከተገኘም መጻሕፍቱ እንደገና ተሻሽለው ሲዘጋጁ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸውን ጉዳዮች ለመጠቆም ያስችላል። ከዚህ በተጨማሪ መጽሐፎቹ እስከሚሻሻሉ ድረስ የቋንቋው መምህራንና ሌሎች ባለድርሻ አካላት ምን ቢያደርጉ የችግሩን መጠን ሊቀንሱት እንደሚችሉ ሀሳቦችን ለመጠቆም ያስችላል።

ይህ ጥናት በዘጠነኛና አስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች አንብቦ የመረዳት ክሂል ጥያቄዎች ላይ ብቻ ያተኮረ ነው። ስለዚህ ሌሎቹ ሦስቱ ክሂሎችና የሰዋስውና የስነ ጽሑፍ ትምህርቶች መልመጃዎች አዘገጃጀት በዚህ ጥናት አልታዩም። ከአንብቦ መረዳትና ከጥልቅና ሰፊ ንባብ ውጭ ያሉ ንባብ ነክ ጉዳዮችም ቢሆኑ በዚህ ጥናት አልተመረመሩም።

## የተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ፤ አንብቦ የመረዳት ክሂሎች

አንድን ጽሑፍ አንብቦ መረዳት ማለት በጽሑፉ የቀረቡ ሀሳቦችንና መረጃዎችን ስኬታማ በሚባል ደረጃ መለየትና ጠቃሚ የሆኑትን የመምረጥ ችሎታ ነው (ግርሌት፣1996)። ተዘውትረው ሊነበቡ የሚችሉ ዋነኛ የጽሑፍ(ቴክስት) አይነቶችም፤ረጅም ልቦለዶች፣ አጫጭር ልቦለዶች፣ተረቶች፣ወጎች፣የዕለት ማስታወሻዎች፣የሕይወት ታሪኮች፣ ተውኔቶች፣ ግጥሞች፣ደብዳቤዎች፣ ፖስትካርዶች፣ ማስታወቂያዎች፣ማስተዋወቂያዎች(Advertisements)፣ የጋዜጦችና መጽሄቶች ዓምዶች (ለምሳሌ ርዕሰ አንቀጾች፣ መጣጥፎች፣ ሪፖርቶች፣ ማስታወቂያዎች) ፣የምርምር ስራዎች፣ የመማሪያ መጽሐፎች፣ ሕጎች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ፖስተሮች፣ ሰንጠረዦች፣ ካርታዎች፣ ግራፎች፣ ስዕሎችና የመሳሰሉት ናቸው (ግርሌት፣ 1996፤ኩታ፣2008)።
የቋንቋ ትምህርት አንዱ ዓላማ ተማሪዎችን ለተሻለ የቋንቋ አጠቃቀም ችሎታ ማዘጋጀት ነው። በአማርኛ ቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች በአፍ መፍቻም ሆነ በ፪ኛ ቋንቋነት አንብቦ የመረዳት ክሂሎችን የሚማሩበት አንዱ ዓላማም በተማሪነትና ከተማሪነት ጊዜ በኋላ በህይወታቸው በእነዚህ ክሂሎች በአግባቡ መገልገል እንዲችሉ ለማድረግ ነው። በቀዳሚው ክፍል እንደተጠቆመው አንብቦ መረዳት የሚለው በውስጡ በርካታ ንዑሳን ክሂሎች የተካተቱበት ክሂል ነው። እነዚህን ክሂሎች ለማዳበር ደግሞ ተማሪዎች የተለያዩ መልመጃዎች እየቀረቡላቸው በግል፣ በጥንድና በቡድን እየሰሩ መለማመድ ይኖርባቸዋል (ኩታ፣ 2008፤ግርሌት፣1996)።
ቀጥሎ እነዚህን ክሂሎች እያንዳንዳቸውን በተናጠል በማንሳት በአጭር በአጭሩ ለመቃኘት ተሞክሯል።

**አሰሳና ግርፍ ንባብ** (Scanning & Skimming)

በትምህርት ቤት በንባብ ትምህርት እንዲዳብሩ ከሚጠበቁ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች መካከል ሁለቱ አሰሳና ግርፍ ንባብ የሚባሉት ብልሃቶች/ክሂሎች ናቸው። አሰሳ ከአንድ ጽሑፍ ውስጥ የተወሰኑ ዝርዝር መረጃዎችን በፍጥነት ንባብ ፈልጎ የማግኘት ክሂል ነው (ኩታ፣ 2008)። ግርፍ ንባብ በተወሰነ መልኩ የአሰሳ ንባብን ባህሪ የሚጋራ ይመስላል። ምክንያቱም ይኸኛውም ዝርዝር መረጃ ለመፈለግ ባይሆንም በፍጥነት የሚከናወን አነባበብ ነው። ልዩነታቸው ይኸኛው ዝርዝር መረጃ ለመፈለግ ሳይሆን የጽሑፉን አጠቃላይ ሀሳብ/መንፈስ ለመረዳት የሚካሄድ አነባበብ መሆኑ ነው። በኩታ (2008) ስራ እንደተገለጸው በህይወት ውስጥ ሰዎች አንድን ጽሑፍ የሚያነቡበት ምክንያት ዝርዝር መረጃዎችን በአሰሳ ንባብ ለመለየት ወይም የጽሑፉን መንፈስ ወይም ጽሑፉ ምን ምን አጠቃላይ ጉዳዮችን እንደሚያነሳ በግርፍ ንባብ ለመለየት ሊሆን ይችላል። በዚህ ምክንያት ተማሪዎች የተለያዩ መልመጃዎችን እየሰሩ በአሰሳና በግርፍ ንባብ በፍጥነት መረጃን/ሀሳብን የመፈለግ ክሂላቸውን

እንዲያዳብሩ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን እየሰሩ መለማመድ ይጠበቅባቸዋል። ለዚህ ደግሞ የመማሪያ መጻሕፍት አዘጋጆች ከፍተኛ ኃላፊነት አለባቸው። ጥያቄዎቹም በአሰሳ ንባብ ቁልፍ ቃላትን፣ ስሞችን፣ ድርጊቶችን፣ ዓመተ ምህረቶችን ወዘተ. በፍጥነት እያነበቡ እንዲለዩ/ እንዲያመለከቱ የሚያበረታቱ፣በግርፍ ንባብ ደግሞ የሚነበበውን ጽሑፍ አጠቃላይ ሀሳቦች/ጉዳዮች እንዲሁ እንዲለዩ የሚያለማምዱ ሊሆኑ ይገባቸዋል። በእርግጥ እንዲህ ያሉ ጥያቄዎች በብዛት ሊገኙ የሚገባቸው በዝቅተኛ የክፍል ደረጃዎች ላይ ነው። በዘጠነኛና በአስረኛ ክፍል ደረጃ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸው ከፍተኛ ደረጃ የማሰብና የማስተዋል ችሎታን የሚጠይቁ ሌሎች ጠለቅ ያሉ የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ጥያቄዎች ናቸው (ትምህርት ሚኒስቴር፣2010 ፤ብሉም፣1956፤ ናታል፣1996፤ግርሌት፣ 1996፤ራኒ እና ሌሎች፣ 2004፤ ሙንዘንሜር እና ሩቢን፣ 2013)።

**ቃላትን በዐውድ መረዳት** (Words in context)

አንድ አንባቢ ከዚህ ቀደም የማይታወቁ/ያልተለመዱ(unfamiliar) ቃላት ሲያጋጥሙት ፍቻቸውን እንዲፈልግ የሚጠበቀው መዝገበ ቃላትን በመመልከት ሳይሆን ዐውዳዊ ፍንጮዎችን በመጠቀም ነው(ሜዘርና ሚካርቲ፣2005)። ዐውድን በመጠቀም ከዚህ በፊት የማይታወቁ ቃላትን ፍች ለመረዳት ከሚያስችሉ ቴክኒኮች መካከል በስፔር(2006)፣ሜዘርና ማካርቲ(2005) ስራዎች እንደቀረበው አንዳንዶቹ የሚከተሉት ናቸው፤

*ብያኔ (Definition)*
አንዳንድ ጊዜ ደራስያን በጽሑፋቸው ውስጥ ለተጠቀሙበት እንግዳ (ያልተለመደ) ቃል፣ ቃሉ በገባበት ዓረፍተ ነገር ወይም በቀጣዮቹ ዓረፍተ ነገሮች ውስጥ አንድ ቦታ ላይ ብያኔ ይሰጣሉ። አንባቢዎችም እንዲህ ያለ፣ ያልተለመደ ቃል ሲያጋጥማቸው የቃሉን ፍች የተሰጠውን ብያኔ በማስተዋል ለመረዳት መሞከር ይጠበቅባቸዋል (ሜዘርና ማካርቲ፣2005)። የንባብ ትምህርትም በዚህ መንገድ ተማሪዎች የቃላትን ዐውዳዊ ፍች ከተሰጣቸው ብያኔ በመነሳት የመረዳት ክሂላቸውን ለማዳበር የሚያስችሉ መልመጃዎችን ማካተት ይኖርበታል ማለት ነው።

*ተመሳሳይ ፍች (Synonym)*
በጽሑፍ ውስጥ ለሚገኝ እንግዳ (ያልተለመደ) ቃል ተመሳሳይ ፍች ያለው ሌላ ቃል/ሀረግ በዓረፍተ ነገሩ ውስጥ ሌላ ቦታ ላይ ሊገኝ ይችላል። ሁለቱን በማዛመድ ያልተለመደ ቃልን ፍች መረዳት ሌላው የቃላትን ፍች ከዐውድ የመማሪያ መንገድ ነው። በመማሪያ መጻሕፍት ውስጥ የሚቀርብ የቃላት ትምህርትም እንዲህ ያለ የቃላትን ፍቺ ከዐውድ የመማሪያ መልመጃዎችን ሊያካትት ይገባዋል።

*ተቃራኒ ፍች (Antonym)*
አንዳንድ ጊዜ ደግሞ የአንድን ቃል ፍች በዚያው ዓረፍተ ነገር ውስጥ የሆነ ቦታ ላይ የሚገኝን ተቃራኒ ፍች የያዘ ቃል/ሀረግ መነሻ በማድረግ መረዳት ይቻላል።

*ምሳሌዎች (Examples)*
አንዳንድ ጊዜ በሚነበበው ጽሑፍ ውስጥ የተሰጡ ምሳሌዎች የአንድን ቃል ዐውዳዊ ፍች ለመረዳት ፍንጮ ይሰጣሉ።

*ገለፃ /ማብራሪያ (Explanation)*
አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ፀሐፊው በጽሑፉ ውስጥ የተጠቀመበትን እንግዳ ቃል ምንነት የሚያብራራበት ሁኔታ አለ። በዚህ ጊዜ የጽሑፉ አንባቢዎች ማብራሪያውን በማስተዋል የቃሉን ፍች መረዳት ይጠበቅባቸዋል።

*ስለ ርዕሰ ጉዳይ የሚኖር ዕውቀት (Knowledge of Subject)*
ደራሲው የተጠቀመባቸውን እንግዳ/ያልተለመዱ ቃላት ፍች ለመረዳት የሚያግዝ ሌላው መንገድ አንባቢዎቹ ስለርዕሰ ጉዳዩ የሚኖራቸው የቀደመ ዕውቀት ነው።

*አጠቃላይ ዐውድን መጠቀም (Using General Context)*
አንዳንድ ጊዜ ቃሉ የገባበት ዓረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ ስለቃሉ ፍች ፍንጮ የማይሰጥ ሊሆን ይችላል። በዚህ ጊዜ የጽሑፉን አጠቃላይ ዐውድ በመጠቀም የቃሉን ፍች ለመረዳት መሞከር ያስፈልጋል። ይህም በትምህርትነት እየቀረበ ሊዳብር የሚገባው ክሂል ነው (ኩታ፣2008)።

## ርዕሰ ጉዳይን፣ ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችንና የደራሲውን ዓላማ መረዳት

ለሕይወት ከሚያስፈልጉና በትምህርት ሊዳብሩ ከሚገባቸው የአንብቦ መረዳት መሠረታዊ ክሂሎች መካከል ርዕሰ ጉዳይን፣ ዋና ሀሳቦችን፣ዝርዝር መረጃዎችንና የደራሲውን ዓላማ መለየት/መረዳት መቻል፣ የሚሉት ይገኙበታል (ሜዘርና ማካርቲ፣ 2005)። እንዲህ ባለ አንብቦ የመረዳት ተግባር ተማሪዎች የሚከተሉትን ችሎታዎች እንዲያዳብሩ ይጠበቃል፤

*ርዕሰ ጉዳይን /Topic/ መለየት*
እንደሜዘርና ማካርቲ (2005) ገለጻ አብዛኛዎቹ አንቀጾች ስለአንድ ርዕሰ ጉዳይ ወይም ርዕስ የሚያትቱ /የሚናገሩ/ ናቸው። በአንቀጽ ውስጥ ርዕሰ ጉዳይ ተገልጾ የሚገኘውም በአንድ ቃል ወይም ሀረግ ነው። ርዕሰ ጉዳይን ለመለየትም "አንቀጹ የሚገልጸው ስለምንድን ነው? የሚል ጥያቄ መጠየቅ ነው። ርዕሰ ጉዳይ የሚባለው ለዚህ ጥያቄ የሚሰጠው መልስ ነው ማለት ነው።

*የአንቀጾችን ዋና ዋና ሀሳብና መገኛ ቦታ መለየት*
ማንኛውም አንቀጽ በአንድ ዋና ሀሳብ ላይ በሚያትቱ ዓረፍተ ነገሮች የሚዋቀር ነው። አንድ አንቀጽ ጥሩ አንቀጽ ነው የሚባለውም በአንቀጹ ውስጥ የሚገኙ ሁሉም ዓረፍተ ነገሮች ዋናውን ሀሳብ የሚያስፋፉ ሆነው ሲገኙ ነው። ዋናውን ሀሳብ ለማግኘት/ለመለየትም "ደራሲው በዚህ አንቀጽ ስለርዕሰ ጉዳዩ ምን ቁልፍ ነጥብ እንዳውቅ ነው የሚፈልገው?" የሚለውን ጥያቄ መጠየቅ ነው (ሜዘርና ማካርቲ ፣2005)። የአንድ አንቀጽ ዋና ሀሳብ በአንቀጹ ውስጥ በአንድ ዓረፍተ ነገር በግልጽ ተጽፎ ሊገኝም ላይገኝም ይችላል። በጽሑፉ ውስጥ የሚገኝ ከሆነም የሚገኝበት ቦታ የተለያየ ነው። ለምሳሌ በአንቀጽ መነሻ ላይ ወይም መድረሻ ላይ ወይም መሐል ላይ ሊገኝ ይችላል። አንዳንድ ፀሀፊዎች ዋናውን ሀሳብ በግልጽ በአንቀጹ ውስጥ አጠቃላይ ሀሳቡን ጨምቆ በያዘ ዓረፍተ ነገር ጽፈው ላያቀርቡም ይችላሉ። ነገር ግን ሁሉም ዝርዝር ሀሳቦች ስለአንድ ሀሳብ ብቻ እንዲያትቱ በማድረግ ዋናውን ሀሣብ አንባቢው በራሱ ጥረት እንዲረዳው ያደርጋሉ። በሁለቱም ሁኔታ አንባቢዎች የአንቀጾቹን ዋና ዋና ሀሳብ መለየት ይጠበቅባቸዋል። ወደኋላ እንደምንመለከተው ይህም በትምህርት ሊዳብር የሚችል ክሂል ነው። የየአንቀጹን ዋና/አጠቃላይ ሀሣብ የያዘ ዓረፍ ተነገር በየአንቀጹ ውስጥ የሚገኝ በሚሆንበት ጊዜ አንድ አንባቢ ዋናውን ሀሳብ መረዳቱን የሚያረጋግጠው ዋናውን ሀሳብ የያዘውን ዓረፍተ ነገር መለየት ሲችል ነው። የአንድ አንቀጽ ዋና ሀሳብ በአንቀጽ ውስጥ ካልሰፈረ ግን ቁልፍ የሆኑ ዝርዝር ሀሳቦችን መነሻ በማድረግ የአንቀጽ ዋና ሀሳብ ምን እንደሆነ መረዳት የአንባቢው ድርሻ/ኃላፊነት ይሆናል።

*ዋነኛና ንዑሳን ደጋፊ ሀሳቦችን መለየት/መረዳት*
አንቀጽን በመረዳት ረገድ 3ኛው ጉዳይ ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት መቻል ነው። ዝርዝር ሀሳቦች /details/ የሚባሉትም ዋናውን ሀሳብ የሚያስፋፉ/የሚደግፉ ዓረፍተ ነገሮች ናቸው(ሜዘርና ማካርቲ ፣2005፤ስፔርስ፣2006)። በአንቀጽ ውስጥ ከሚገኙ ዓረፍተ ነገሮች ዋናውን ሀሳብ የሚይዘው ዓረፍተ ነገር የሚይዘው ሀሳብ ሰፊ ሲሆን በአንፃሩም ሌሎች ዓረፍተ ነገሮች ከዋናው ሀሳብ ወይም ከሀይለ ቃሉ የሚመነጩና ዋናውን ሀሳብ የሚያስፋፉ/አፍታተው የሚያቀርቡ ጠባብ ሀሳቦችን የሚይዙ ዝርዝር ነጥቦች ናቸው። እነዚህ ዝርዝር ነጥቦች/ሀሳቦች የሚባሉት ብዙ ጊዜ ምሳሌዎች ወይም እውነታዎች፣ ምክንያቶች፣ ማብራሪያዎች ወዘተ. ሊሆኑ ይችላሉ። በአንዳንድ የንባብ ክሂልን የሚያስረዱ መጻሕፍት (ለምሳሌ በሚዘርና ማካርቲ 2005 ስራ) እነዚህ ዝርዝር ሀሳቦች ዋነኛ (major details) እና ንዑሳን ሀሳቦች (minor details) ተብለው እንደገና በሁለት ሊከፈሉ ይችላሉ። ዋነኛ ዝርዝር ሀሳቦች የሚባሉት ከዋናው ሀሳብ የሚመነጩና ከዚህ ዋና /main/ ሀሳብ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው ሀሳቦች ናቸው። ንዑሳን ሀሳቦች የሚባሉት ደግሞ እነዚህን ዋነኛ ዝርዝር ሀሳቦች የሚያስፋፉ/የሚደግፉ ሀሳቦችን የያዙ ዓረፍ ነገሮች ናቸው (ሜዘርና ማካርቲ፣2005)። የሚከተለው ምስል ከላይ የቀረበውን ማብራሪያ ግልጽ ሊያደርገው ይችላል፤

ዋና ሀሳብ /Main idea/

ቁልፍ/ ዋነኛ ዝርዝር ሀሳቦች /Major details/

⇒ ንዑሳን ዝርዝር ሀሳቦች

ቁልፍ/ዋነኛ ዝርዝር ሀሳብ

⇒ ንዑሳን ዝርዝር ሀሳቦች

(ምንጭ፣ ሜዘርና ማካርቲ፣2005)

*የደራሲውን ዋና ዓላማ መለየት* (Determing the Author's Purpose)
አብዛኛዎቹ የታሪክ፣ የወግ፣ የመጣጥፍ ወይም የግጥም ፀሐፊዎች/ደራስያን አንድን ጽሑፍ የሚጽፉት ቢያንስ አንድ አጠቃላይ ዓላማ ላይ ተመስርተው ነው። ይህን ዓላማ አንባቢው እንዲለይ የሚያስችሉ ፍንጮዎችም ጽሑፉ ውስጥ ይኖራሉ። ዓላማውን ለመለየትም ደራሲው ይህን ጽሑፍ የጻፈው ለምን ዓላማ ነው? የሚል ጥያቄ መጠየቅ ነው። አንባቢው እንዲህ ያለ ጥያቄ ሲያነሳ ሊያገኘው የሚችለው አጠቃላይ ዓላማ መረጃ ለማስተላለፍ ወይም ለማዝናናት ወይም ሀሳብን ለማስቀየር/ለማሳመን (to persuade) ከሚሉት አንዱ መሆኑን ያረጋግጣል (ሜዘርና ማካርቲ ፣2005)።

መረጃ ለማስተላለፍ/ለመስጠት ከሚጽፍ ደራሲ፣አንባቢ ሊያገኝ የሚችለው/የሚያገኘው ዕውቀት/ ወይም መረጃ ነው። እንዲህ ያለ ጽሑፍ የሚጽፍ ደራሲ ገለልተኛ (Objective, Neutral) ሆኖ ነው፤የራሱን ሀሳብና ስሜት ጣልቃ አያስገባም። ነባራዊ እውነታን እንዳለ ሳያጋንን ወይም ሳያንኳስስ ለመግለጽ ነው የሚሞክረው። ዓላማውን ማዝናናት ላይ ያደረገ ጽሑፍ ደግሞ ለአንባቢ ታሪክ ሲነገር ወይም አንድን ጉዳይ ሲተርክ ለዛ የተላበሰና የአንባቢውን ስሜት እንዲኮረኩር አድርጎ ነው።

ለአንባቢው ምናብ የሚቀርብ አፃፃፍ ነው። ሦስተኛው አይነት ዓላማ አንባቢን በአንድ ጉዳይ ላይ ለማሳመን ወይም የደራሲው/የፀሐፊው አቋም ደጋፊ/ተጋሪ እንዲሆን ለማድረግ የሚፃፍ ድርሰት ነው /ስፔርስ፣2006፤ሜዘርና ማካርቲ፣2005)። ይህ አይነት አጻጻፍ በአማርኛ አመዛዛኝ/ አከራካሪ ድርሰት በመባል የሚታወቅ ነው።

በእርግጥ እነዚህ (በ2.3.4 ስር የተጠቀሱት) በአጠቃላይ /General/ ዓላማነት ይታወቁ እንጂ እንደገና ወደተለያዩ ንዑሳን/ ዝርዝር ዓላማዎች ተሸንሽነው ሊቀርቡም ይችላሉ። ለምሳሌ አንድ ጽሑፍ/ ድርሰት አንድ ዋናና አንድ ወይም ከአንድ በላይ ንዑስ/ዝርዝር ዓላማዎች ሊኖሩት ይችላሉ (ሜዘርና ማካርቲ፣2005/። አንድ አንባቢ ጥሩ አንባቢ ነው የሚባለው በሚያነባቸው ጽሑፎች ውስጥ የሚገኙ ርዕሰ ጉዳዮችን፣ ዋና ዋና ሀሳቦችን፣ ቁልፍ/ዋነኛ ንዑሳን ዝርዝር ሀሳቦችንና የደራሲውን ዓላማ የሚረዳ ሆኖ ሲገኝ ነው። እነዚህ አንብቦ የመረዳት ችሎታዎች በቀላሉ ሊዳብሩ የሚችሉት ደግሞ በትምህርት ገበታ ትኩረት ተሰጥቷቸው ሲቀርቡ ነው።
ስለዚህ በቋንቋ ትምህርት ተማሪዎች እነዚህን አንብቦ የመረዳት ክሂሎች ለማዳበር እንዲችሉ የተለያዩ መልመጃዎችን እየሰሩ መለማመድ ይኖርባቸዋል። መልመጃዎቹም ተማሪዎች ርዕሰ ጉዳዮችን፣ ዋና፣ ዋነኛና ንዑሳን ዝርዝር ሀሳቦችንና የደራሲውን ዓላማ እየለዩ እንዲለማመዱ የሚያስችሉ ሊሆኑ ይገባቸዋል።አቀራረባቸውም ምርጫ በሚሰጡና ምርጫ በማይሰጡ ጥያቄዎች ሊሆን ይችላል። ለምሳሌ ፦

- የእያንዳንዱን አንቀጽ ርዕሰ ጉዳይ ግለፁ።
- የአንቀጽ አንድን፣ ሦስትንና ስድስትን ሀሳብ/ሀይለ ቃል የያዙ ዓረፍተ ነገሮችን ለዩ።
- በአንቀጽ አምስት .... የሚገኙ ሁለት ቁልፍ/ዋነኛ/ ዝርዝር ሀሳቦችን አውጡ።
- የአንቀጽ .... ጠባይ በምስል አሳዩ።
- በሚከተሉት አንቀጾች ውስጥ ዋናውን ሀሳብ የያዙ ዓረፍተ ነገሮች የሚገኙት በተለያዩ ቦታዎች ላይ ነው።በየአንቀጹ ዋናውን ሀሳብ የያዘውን ዓረፍተ ነገር ስንተኛው እንደሆነ ቁጥሩን በመፃፍ አመልክቱና ምክንያታችሁን አስረዱ፤ የአንቀጾቹን ጠባይ/ ቅርጽም በምስል አሳዩ፤ በሚሉ አጠያየቆች ተማሪዎችን ማለማመድ ይቻላል።
- ከዚህ በተጨማሪ ምርጫ ሰጭ ጥያቄዎችን በመጠቀምም የተማሪዎችን ርዕሰ ጉዳይ፣ ዋና ሀሳብ፣ ዋነኛና ንዑስ ዝርዝር ሀሳቦችና የደራሲውን ዓላማ የመለየት ክሂል ማለማመድ ይቻላል። ለምሳሌ ርዕሰ ጉዳዮችን፣ዋና ሀሳቦችን፣ዝርዝር ሀሳቦችንና ዓላማዎችን የያዙ ዓረፍተ ነገሮችን አቅርቦ፣ርዕሰ ጉዳይ የሆኑት "ር" ዋና ሀሳቦችን "ዋሀ" ዝርዝር ሀሳቦችን "ዝሀ" የደራሲውን ዓላማ "ዓ" እያላችሁ አመልክቱ፤የሚሉ አይነት መልመጃዎችን ማካተትም ይቻላል (ሜዘርና ማካርቲ፣2005፣82)።

*ያነበቡትን በራስ አባባል መግለጽ /paraphrasing/*

የተማሪዎችን ጽሑፍ አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበር በተለይም የጽሑፉን ወይም የአንቀጾችን ዋና ዋናና ዝርዝር ሀሳቦችን በቀላሉ የመረዳት ችሎታ ከፍ ለማድረግ ሲያነቡ የተረዱትን በራሳቸው አባባል እንዲገልጹ የማድረግ አንዱ ስልት ነው (ሜዘርና ማካርቲ ፣2005) ።በራስ አባባል መግለጽ ማለትም በሚነበበው ጽሑፍ ውስጥ ያሉ ቁልፍ ቃላትና ዋና ዋና ሀሳቦችን መረዳትና የተረዱትን በራስ ቋንቋ መግለጽ ማለት ነው (ሜዘርና ማካርቲ ፣2005)። ይህን ክሂል ለማዳበር የሚዘጋጁት ጥያቄዎችም፤

- የሚከተለውን አንቀጽ አንብቡና የተረዳችሁትን በራሳችሁ አባባል ግለጹ።
- የሚከተለውን ተረት /ታሪክ ወይም ጽሑፍ ሀሳብ በራሳችሁ ቋንቋ ግለፁ።
- የሚከተለውን አንቀጽ (ሀይለ ቃል የሌለው /implied/ ማለት ነው) ዋና ሀሳብ ተናገሩ/ ግለፁ፤ የሚሉ አይነቶች ሊሆኑ ይችላሉ።
- በምንባቡ ውስጥ የቀረቡ ሀሳቦችን በሌላ አባባል በመግለጽም የምርጫ፣የማዛመድ፣ የእውነት/ ሀሰት በሉ ጥያቄዎችን አዘጋጅቶ ተማሪዎች እንዲመልሱ በማድረግ አንድን ሀሳብ በተለያየ አባባል የመግለጽ ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማለማመድ ይቻላል( ስፔርስ ፣2006፤ሜዘርና ማካርቲ፣2005)።

### ማሳጠር (Summary)

በንባብ ክሂል ትምህርት ሊዳብር የሚገባው ሌላው ክሂል ያነበቡትን አሳጥሮ የመግለጽ ችሎታ ነው።አሳጥሮ የመፃፍ ሂደት በተወሰነ ደረጃ በራስ አባባል ከመግለጽ ጋር ይመሳሰላል። ምክንያቱም በዚህኛውም በራስ አባባል የመግለጽ ነገር አለበት። ሆኖም በማሳጠር ሂደት አጥረው የሚፃፉት ዋና ዋናና ቁልፍ የሚባሉ ዝርዝር ሀሳቦች ናቸው።ትኩረት የሚሰጠው ለማንኛውም ዓረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ ሳይሆን ለዋና ዋና ሀሳቦች ነው። ይህንም በራስ አባባል መግለጽንና ማሳጠርን የተለያዩ ተግባራት/ክሂሎች ያደርጋቸዋል (ሜዘርና ማካርቲ ፣2005)።

ማሳጠር/አሳጥሮ መፃፍ ሰዎች በተማሪነት ዘመናቸውና ከትምህርት በኋላ በስራ መስክ በስፋት የሚገለገሉበት ጠቃሚና አስፈላጊ ክሂል ነው። ቀደም ሲል በተጠቀሱት ምሁራን እንደተገለጸው አንድ ጽሑፍ አጥሮ በሚጻፍበት ጊዜ ዋና ዋና ሀሳቦችና ቁልፍ/ዋነኛ የሆኑ ዝርዝር ሀሳቦች (major details) ላይ ማተኮርን ይጠይቃል፤ንዑሳን ዝርዝር ሀሳቦችን ማካተት አያስፈልግም። በዚህ የተነሳ አጥሮ የሚፃፈው ጽሑፍ ከዋናው ጽሑፍ በመጠን ያንሳል። ሌላው ቁም ነገር አንድ ጽሑፍ አጥሮ በሚፃፍበት ጊዜ አጥሮ የሚፃፈው ጽሑፍ ከዋናው ጽሑፍ ፀሐፊ አመለካከት አንፃር እንጂ ከአሳጣሪው አንፃር እንዳልሆነ ልብ ማለት ይገባል። ተማሪዎችም አሳጥረው እየፃፉ ሲለማመዱ በዚሁ አስተሳሰብ መሠረት እንዲሆን ማድረግ ያስፈልጋል። ከዚህ በተጨማሪ አጥሮ በሚፃፈው ጽሑፍ ውስጥ አሳጥሮ የሚጽፈው ሰው ሀሳቦችና አመለካከቶች አለመካተታቸውን ማረጋገጥ ያስፈልጋል(ሜዘርና ማካርቲ፣2005፣100)።

*ቃላዊና/ ወይም ሰዋስዋዊ አያያዦችን/መሸጋገሪዎችን መረዳት /Understanding Lexical and/ or Grammatical Cohesion/*

አንቀጾች አንድነት ብቻ ሳይሆን ግጥምጥምነት /Cohesion/ ያላቸው ሆነው ሊዋቀሩ/ሊፃፉ ይገባቸዋል። ይህንም በመረዳት ደራስያን ድርሰት በሚጽፉበት ጊዜ ከአንዱ ዓረፍተ ነገር ወደ ቀጣዩ እንዲሁም ከአንዱ አንቀጽ ወደ ሌላው አንቀጽ የሚደረገው ሽግግር የማይጎረብጥና የሀሳብ ፍሰት ያለው እንዲሆን የቃላዊና/ሰዋስዋዊ አያያዦችን/መሸጋገሪያ ስልቶችን ይጠቀማሉ። አንባቢዎችም ሲያነቡ ደራሲዎቹ በድርሰቶቻቸው ውስጥ ያካተቷቸው አንቀጾችና በአንቀጾቹ ውስጥ ያሉ ዓረፍተ ነገሮች እንዴት እንደተጣመሩና ምን አይነት የመሸጋገሪያ ቃላትና ሀረጋትን እንደተጠቀሙ በቀላሉ እየለዩና እየተረዱ ማንበብ ይኖርባቸዋል።

በንባብ በተለይም በአንብቦ መረዳት ክሂሎች ላይ የጻፉ ምሁራን እንደሚያስረዱት ሰዎች ሲያነቡ ለመሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋት የተለየ ትኩረት መስጠታቸው የሚያነቡትን ጽሑፍ በቀላሉ እንዲረዱ ያስችላቸዋል። ለአንባቢ በዓረፍተ ነገሮችና በአንቀጾች መካከል ያሉ የሀሳብ ግንኙነቶችን/ቁርኝቶችን የሚያሳዩና ጽሑፉ የሀሳብ ፍሰት እንዲኖረው የሚያደርጉት እነዚህ የመሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋት የሚባሉት ናቸው። ልክ ጎበዝ የሚባል ሾፌር መኪና ሲያሽከረክር ፊት ለፊት ያለውን መንገድ በጥንቃቄ መመልከትን እንደሚማር ሁሉ ጥሩ አንባቢም የሚያነበውን ጽሑፍ የመሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋት የተለየ ትኩረት የመስጠት ክሂሉን ማዳበር ይኖርበታል። ይህም የሚያነበው ጽሑፍ ግልጽ እንዲሆንለትና አንብቦ የመረዳት ክሂሉ ከፍ እያለ እንዲሄድ ያስችለዋል (ሜዘርና

ማካርቲ፣2005፤ሲምፕሰን፣1997)።

ደራስያን ከዓረፍተ ነገር ዓረፍተ ነገር እና ከአንቀጽ አንቀጽ ሽግግር የሚፈጥሩባቸው ስልቶችም፤1ኛ.መሸጋገሪያዎችን በመጠቀም (Using transitions)፣2ኛ. ቁልፍ ቃላትን በመደጋገም (By repeating key words) እና 3ኛ. ተውላጠ ስሞችን በመጠቀም (Using Pronouns) በሚባሉ ሦስት ዋና ዋና ምድቦች ሊከፈሉ ይችላሉ (ሜዘርና ማካርቲ ፣2005፤ሲምፕሰን፣1997)።

*መሸጋገሪያዎች* (Transitions)
አንድ ደራሲ ዓረፍተ ነገርን ከዓረፍተ ነገር፣አንቀጽን ከአንቀጽ ለማያያዝ የሚጠቀምበት መሸጋገሪያ አንድ ቃል ወይም ሐረግ ሊሆን ይችላል። በዚህ ረገድ በተለያዩ ክፍሎች(Categories) የሚመደቡ በርከት ያሉ የመሸጋገሪያ ቃላትና ሐረጋት ያሉ ሲሆን ከእነዚህ መካከል 1ኛዎቹ ምድብን/ክፍልን የሚያሳዩ ናቸው። 2ኛዎቹ ምክንያትንና ውጤትን የሚያመለክቱ ናቸው፤ (ለምሳሌ፤ በዚህ ምክንያት፣ ስለዚህ፣ በመሆኑም፣ ምክንያቱም)። 3ኛዎቹ አወዳዳሪ /ተመሳስሎን የሚያሳዩ መሸጋገሪያዎች ናቸው። ለምሳሌ፤ ሁሉም፣ እና፣ ሁለቱም፣ ሲወዳደር፣ ልክ፣ በተመሳሳይ ሁኔታ)። 4ኛዎቹ አነጻጻሪ (ልዩነትን የሚያሳዩ መሸጋገሪያዎች፤ (ምሳሌ፤ ቢሆንም፣ ግን፣ ነገር ግን፣ ቢሆንም እንኳ፣ በተቃራኒው፣በአንፃሩ፣ በሌላ በኩል)፣ 5ኛዎቹ ሂደትን ወይም ቅደም ተከተልን ወይም ደረጃን የሚያመለክቱ ናቸው፤(ምሳሌ በመጀመሪያ /መጀመሪያ፣ አንደኛ፣ ሁለተኛ፣ ሦስተኛ... ቀጥሎ፣ አሁን፣ ቀደም ብሎ፣ ከዚያም፣ በፊት፣ በኋላ፣ ከዚያ በፊት፣በመጨረሻ (ም) ባለፈው ዕለት/ሣምንት/ ወር፣ በ... ዓ.ም፣ ወደኋላ፣ ወዲያው፣ እስከ፣ መቼ ወዘተ.)። 6ኛዎቹ አጽንኦትን የሚያመለክቱ፤(ምሳሌ፤ በእርግጥ፣ በአብዛኛው፣ ያለጥርጥር፣ የሚያከራክሩ፣ በእውነት...)። 7ኛዎቹ ምሳሌዎችን የሚያሳዩ (ለምሳሌ፤ በተለይ፣ እነሱም፣ ማስረጃ...)፣ 8ኛዎቹ ማጠቃለያ ቃላትና ሐረጋት (ምሳሌ፤ ስለዚህ፣ ለማጠቃለል፣...) ናቸው።

ቁልፍ ቃላትና ሐረጋትን መደጋገም
ሁለተኛውና በተለይ በዘመናዊ ደራስያን ግጥምጥነትን ለመመስረት/ለመፍጠር የሚጠቀሙበት መንገድ በቀዳሚው ዓረፍተ ነገር ወይም በቀዳሚው አንቀጽ ውስጥ የሚገኙ ቁልፍ ቃላትን /ሐረጋትን በተከታዩ ዓረፍተ ነገር ወይም አንቀጽ ውስጥ ደግሞ በማምጣት ከሀሳብ ሀሳብ ወይም ከዓረፍተ ነገር ወደ ዓረፍተ ነገር የሚሸጋገሩበት ስልት ነው (አማረ፣1976፤ሲምፕሰን 1997፤ስፔርስ፣2006)። በኢትዮጵያ በአማርኛ ለምሳሌ በእነ፤በዓሉ ግርማ፣ሲሳይ ንጉሱ... ስራዎች ጎልቶ የሚታይ አጻጻፍም ነው። ይህ ስልት በመሸጋገሪያነት ከማገልገሉ በተጨማሪ "አንባቢው ከመስመር እንዳይወጣና ትኩረቱን እንደሰበሰበ እንዲቀጥል የሚያስችልም ነው" (ስፔርስ፣2006፣168)።

ስለዚህ እንዲህ ያሉ የመሸጋገሪያ ዘዴዎችን ለተማሪዎች በጥልቀት የሚያስተዋውቁ ትምህርቶችን በማንበብ ትምህርት አሰጣጥ ላይ ማካተት፣አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውን ከማሳደጉ በተጨማሪ ድርሰት ሲጽፉ በተለመዱና የማሰልቸት ጸባይ በሚኖራቸው መደበኛ አያያዦች ብቻ ሳይሆን ቁልፍ ቃላትና ሐረጋትን በመደጋገም የመፃፍ ልምድ እንዲያገኙም ያስችሏቸዋል (ሲምፕሰን፣1997፤ ስፔርስ፣2006)።

ተውላጠ ስሞችን በመጠቀም መሸጋገር
ተውላጠ ስሞችን በመጠቀም ከዓረፍተ ነገር ዓረፍተ ነገርና ከአንቀጽ ወደ አንቀጽ መሸጋገርም ሦስተኛውና ሌላው የተለመደ የመሸጋገሪያ ስልት ነው።

በማስተማር ተግባር ተማሪዎችን እነዚህን የመሸጋገሪያ ስልቶች በማስተማር አንብበው የመረዳት ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ለማገዝ የተለያዩ መልመጃዎችን በተለያዩ ስልቶች በመማሪያ መጽሐፎች ውስጥ ማካተት ይገባል። ለምሳሌ የቃላትና ሐረጋትን ዝርዝር አቅርቦ የተሰጡትን ቃላትና ሐረጋት በዓረፍተ ነገሮች/አንቀጾች ውስጥ በተሰጡ ክፍት ቦታዎች ላይ ተገቢውን አያያዥ/መሸጋገሪያ እየመረጡ እንዲጠቀሙ ማድረግ አንዱ ነው። ሁለተኛ በሚያነቡት ጽሑፍ ውስጥ የሚገኙ አያያዦችን ለይተው እንዲያመለክቱና የአያያዦችን ተግባር እንዲገልጹ በመጠየቅ ማለማመድ ይቻላል።

*አንቀጾች የተስፋፉባቸውን ዘዴዎች መለየት*
አንቀጾች የተስፋፉባቸውን ዘዴዎች (ምሳሌ፣ ብያኔ፣ ማወዳደርና ማነፃፀር፣ምክንያትና ውጤት፣ ምስያ ወዘተ.) መለየት አንብቦ መረዳትን ቀላል ከሚያደርጉ መንገዶች አንዱ ነው (ስፔርስ ፣2006፤ሜዘርና ማካርቲ፣2005)። ስለዚህ በተለያዩ የአንቀጽ ማስፋፊያ ዘዴዎች የተስፋፉ አንቀጾች የሚገኙባቸውን ምንባቦች ተማሪዎች እንዲያነቡ፣እንዴት እንደተስፋፉ እንዲለዩና በምክንያት እንዲያስረዱ በማድረግ

አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ የአንብቦ መረዳት ትምህርት አንዱ ትኩረት ሊሆን ይገባዋል(ስፔርስ፣2006፤ግርለት፣1996)። እንዲህ ያሉ መልመጃዎች እንደመሸጋገሪያና ሌሎች የአንብቦ መረዳት ክሂል ትምህርቶች የተማሪዎችን የመፃፍ ክሂል ለማዳበርም በጣም አስፈላጊ ናቸው። መልመጃዎቹም በምርጫ ሰጪና ክፍት አጠያየቆች ሊዘጋጁ ይችላሉ (ስፔርስ፣2006)።

*ላነበቡት ትርጓሜ መስጠት (Interpreting what is Read)*
ያነበቡትን መተርጎም በሚለው ክፍል አንድምታ("ኢንፈር"ማድረግ)፣ዘይቤያዊ አገላለጾችን መረዳትና የደራሲውን ድምጸት መለየት የሚሉት ክሂሎች ዋነኛዎቹ ናቸው።

ማውጣጣት(Inference) በጽሑፍ ውስጥ በግልጽ ያልቀረቡ/ድብቅ ሀሳቦችንና መረጃዎችን (Hidden Meaning) መረዳት
አንድምታ አንድን ጽሑፍ መስመር በመስመር ለእያንዳንዱ ቃል፣ ሀረግና ዓረፍተ ነገር ሳይቀር የተለየ ትኩረት እየሰጡ በማንበብ፣ በጽሑፉ ውስጥ የሚገኙ አንዳንድ ፍንጮዎችን በመጠቀም ጭምር በግልጽ ያልቀረቡ ሀሳቦችንና መረጃዎችን የመረዳት ክሂል ነው። ምክንያቱም አንድ ደራሲ በሚጽፈው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ያሉ ሁሉንም ነገሮች አያነሳም፣ እንዲያነሳም አይጠበቅም። አንባቢው ስለጉዳዩ ካለው የቀደመ ዕውቀትና በጽሑፉ ውስጥ ከሚያገኛቸው ፍንጮዎች በመነሳት እንዲረዳቸው የሚጠበቁ ሀሳቦች ይኖራሉ። እንዲህ ያሉ ሀሳቦችንና መረጃዎችን የመረዳት ክሂል አንድምታ/"ኢንፈር"የማድረግ ክሂል ይባላል (ኩታ፣2008፤ስፔርስ፣ 2006)። አንድምታ በውስጡ ብዙ ንዑሳን ክሂሎች የሚገኙበት ሲሆን ከእነዚህ መካከል ዋነኛዎቹ እውነታን ከአንድምታ/ከአስተያየት መለየት መተንበይ፣ በምስል የቀረቡ ሀሳቦችን አንድምታ መለየት (ስፔርስ፣2006) የሚሉት ዋነኛዎቹ ናቸው።

እውነታዎችን፣አንድምታዎችንና አስተያየቶችን መለየት
የጥሩ አንባቢ አንዱ መለኪያ በሚያነበው ጽሑፍ ውስጥ የቀረቡ ሀሳቦችን እውነታነት ወይም አንድምታነት ወይም አስተያየትነት መለየትና አስተያየቶችን ከተለያየ አቅጣጫ፣ከቀደመ ዕውቀት፣ ከነባራዊ እውነታዎች ጋር እያገናዘቡ መቀበል ወይም መቃወም የመቻሉ ደረጃ ከፍ ማለት ነው። እውነታ የሚባለውም ሊረጋገግጥ ወይም ሊለካ ወይም ሊመሳከር የሚችል መረጃ ነው። በሌላ በኩል አስተያየት ከእውነታ የሚመነጭ ሆኖ ለማረጋገጥ የሚያስቸግር ሀሳብ ወይም መረጃ ነው። ከሚታወቀው የማይታወቀውን ማወቅ ወይም መረዳት መቻል ነው። ለምሳሌ ባህር ዛፍ ለመጀመሪያ ጊዜ የተገኘው አውስትራሊያ ውስጥ ነው የሚለው ሀሳብ እውነታ/የታወቀ ነገር ነው። ነገር ግን ከዚህ እውነታ በመነሳት "አውስትራሊያ ለባህር ዛፍ ተክል የሚስማማ ቦታ ይመስላል"፣ብሎ መረዳት በአንድምታ የሚረዱት ሀሳብ ወይም አስተያየት ነው (ስፔርስ፣2006)። እንዲህ ያለ ክሂል ሊዳብር የሚችለው በትምህርት ቤት፣ በትምህርት ሲደገፍ በመሆኑ በመማሪያ መጽሐፎች መልመጃዎች ውስጥ ሊካተት ይገባዋል (ኩታ፣2008፤ስፔርስ፣2006)።

መተንበይ/የትንበያ ክሂሎች (Predicting Skills)
ትንበያ አንድ አንባቢ ከሚያነበው ጽሑፍ ጋር መስተጋብር (interaction) የሚፈጥርበት አንድ መንገድ ነው። ትንበያ ማለትም አንድ አንባቢ ሊያነበው ያሰበው ጽሑፍ ወይም እያነበበው ያለው ጽሑፍ ቀጥሎ ምን ምን ጉዳዮችን ሊያነሳ እንደሚችል ማሰብ ወይም መገመት ነው። በሌላ አማርኛ ትንበያ ማለት ለማንበብ የተመረጠውን ጽሑፍ ርዕስ በማየት ጽሑፉ ስለምን ሊገልጽ እንደሚችል፣እንዲሁም የጽሑፉን የተወሰነ ክፍል በማንበብ ቀጥሎ ሊመጣ የሚችለውን እየገመቱ (እየተነበዩ) የማንበብ ሂደት ነው (ኩታ፣2008፤ግርሌት፣1996፤ ናታል፣1996)። ስለዚህ የመማሪያ መጽሐፍ አዘጋጆች በንባብ ትምህርት የተማሪዎችን የመተንበይ ክሂል ለማዳበር የሚያስችሉ ጥያቄዎችን በአግባቡ ሊያካትቱ ይገባቸዋል።

በምስል የቀረቡ መረጃዎችን አንድምታ መረዳት (Making Inferences with Visual Material)
አንድ ጽሑፍ በስዕሎች፣ በካርቱኖች፣በሰንጠረዦች፣ በግራፎች፣ በካርታዎችና ፎቶዎች ተደግፎ ሲቀርብ ማየት የተለመደ ክስተት ነው። ስለዚህ አንድ አንባቢ እንዲህ ያሉ ምስሎችን አንድምታ መረዳት ይጠበቅበታል። በንባብ ትምህርትም ተማሪዎች የተለያዩ ካርቱኖችን፣ ስዕሎችን፣ ግራፎችን፣ ሰንጠርዦችን፣ ካርታዎችን፣ ተመልክተው የምስሎችን አንድምታ የመረዳት ክሂላቸውን የሚያዳብሩ መልመጃዎችን እየሰሩ መለማመድ ይኖርባቸዋል፤ ተግባራቱም በክፍልና በቤት ስራነት ሊሰጡ ይችላሉ (ኩታ፣2008፤ስፔርስ፣2006፣ናታል ፣1996)።

በዘይቤያዊ ቋንቋ የተገለጹ ሀሳቦችን መረዳት

ደራስያን ሀሳባቸውን በተመለዱ ቃላት ብቻ ሳይሆን ከዚህ በፊት የሚሰራባቸውንም ሆነ አዳዲስ ዘይቤያዊ አገላለጾችን በመጠቀም ሲገልጹ ማየት የተለመደ ነገር ነው። አንባብያንም ደራሲዎቹ የተጠቀሙባቸውን ዘይቤያዊ (በተነጻጻሪ፣ በተለዋጭ፣በሰውኛ፣ በምጸት ወዘተ. ዘይቤ የተገለጹ ሀሳቦችን) አገላለጾች እየተረጎሙ መረዳት ይጠበቅባቸዋል። ይህም በትምህርት ሊዳብር የሚገባው ክሂል ነው። ለዚህ ደግሞ ተማሪዎች በተለያዩ ዘይቤዎች የተገለጹ ሀሳቦች የሚገኙባቸው ጽሑፎች እየቀረቡላቸው በዘይቤዎች ተሞሽረው የቀረቡ ሀሳቦችን እየተረጎሙ እንዲለማመዱ ማድረግ ያስፈልጋል (ስፔርስ፣2006፤ሜዘርና ማካርቲ፣2005)።

በመማሪያ መጽሐፎቹ ውስጥ የተማሪዎችን በዘይቤ የተገለጹ ሀሳቦች የመረዳት ክሂል ለማዳበር፤ ተማሪዎች አንቀጾችን እንዲያነቡና በአንቀጾቹ ውስጥ ለሚገኙ ዘይቤያዊ አገላለጾች ዐውዳዊ ፍች እንዲሰጡ የሚያደርጉ ጥያቄዎችን በመስጠት በዘይቤያዊ ቋንቋ የተገለጹ ሀሳቦችን መልዕክት የመረዳት ክሂል እንዲያዳብሩ ማገዝ ይቻላል (ሜዘርና ማካርቲ፣2005)።
በዚህ ጥናት የፈሊጣዊ አነጋገሮችንና የምሳሌያዊ አነጋገሮችን ዐውዳዊ ፍች የሚያለማምዱ መልመጃዎችም በዚህ ዘይቤያዊ ቋንቋ በሚለው ስር እንዲካተቱ ተደርገዋል።

*የመተንተን(Analyzing) ክሂል*
ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሑፍ ከተለያየ አቅጣጫ ለመረዳት፣በጽሑፉ የተካተቱ ጉዳዮችን በተለያዩ ክፍሎች እየበታተኑ የመረዳት ችሎታ ሊያዳብሩ ይገባቸዋል(ግሊንከ፣1976)። ለምሳሌ ተማሪዎች በኢልቦለድ ጽሑፍ፣ በጽሑፉ ውስጥ የቀረቡ ምክንያቶችንና ውጤቶችን፣የፈጠራ ስራን ደግሞ የታሪኩን ክፍሎች፣ገጸባህርያቱን፣ መቼቱን፣ ጭብጡን፣ መዋቅሩን...፣ እየለዩ እንዲተነትኑ በማድረግ የመተንተን ክሂላቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ይቻላል (ኩታ፣2008)።

*የማዛመድ(Connecting) ክሂል*
ንቁ ተማሪዎች ሲያነቡ የሚያገኟቸውን ሀሳቦች/ዕውቀቶች ከራሳቸው ህይወትና ከዚህ ቀደም ካነበቧቸው ጽሑፎች ሀሳቦች ጋር ያገናዝቧቸዋል። ተማሪዎች ያነበቡትን ሁሉ ሳያመዛዝኑ ዝም ብለው የሚቀበሉ እንዳይሆኑ ወይም ሲያነቡ የሚያገኟቸውን ሀሳቦች፣ያስተዋሏቸውን ስሜቶችና ክስተቶች ከራሳቸው ገጠመኝ፣ ሀሳብና አቋም ጋር እያዛመዱ፣ከዚያም በሚያስደስተው እየተደሰቱ፣ሀሳቦችንና መረጃዎችን የማስተዋል ችሎታቸውን እያሻሻሉ መምጣት ይኖርባቸዋል (ግሊንከ፣1976)። ለዚህ ደግሞ ተማሪዎች ያነበቡትን ሁሉ ትክክል ነው ብለው የሚቀበሉ አይነት ሰዎች እንዳይሆኑ በሚያነቧቸው ጽሑፎች ውስጥ የሚያገኟቸውን ዕውቀቶች የመምረጥ፣ የመቀበልና የመቃወም ክሂላቸውን ለማዳበር የሚያስችሏቸው መልመጃዎች እየሰሩ መለማመድ ይኖርባቸዋል። በኢትዮጵያ ይህ ችሎታ በንባብም ሆነ በማዳመጥ ክሂሎች ትምህርት ትኩረት የተነፈገው እንደሆነ የሚያመለክቱ ብዙ ምልክቶች አሉ። ይህም የመማሪያ መጽሐፎቹ በዚህ ረገድ የሰጡትን ትኩረት/ቦታ የመመርመርን አስፈላጊነት ይጠቁማል።

*ቅንበራ/ማቀናበር (Synthesize)*
በከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂልነት ከሚመደቡት ክሂሎች አንዱ ቅንበራ ነው። በንባብ ትምህርት ቅንበራ/ማቀናበር ተማሪዎች በሚያነቡት ጽሑፍ ውስጥ የቀረቡ ፅንሰ ሀሳቦችን፣ ጠቃሚ ዝርዝርና ዋና ዋና ሀሳቦችን በመጭመቅና እነዚህን ሀሳቦች የሆነ ቅርፅ በማስያዝ አደራጅቶ የማቅረብ ክሂልን የማዳበር ሂደት ነው። ተማሪዎች በሚያነቡት ጽሑፍ ውስጥ ያሉ ሀሳቦችን የሆነ ቅርፅ አስይዘው በሚያደራጁበት ጊዜም ከፍተኛ ደረጃ የሚባሉ የማሰብ ክሂሎቻቸውን የግድ ይጠቀማሉ። ይህም ተማሪዎች የጥሩ አንባቢነት ልምድን እንዲያዳብሩ ይረዳቸዋል (ኩታ ፣2008፣84)።

*ግምገማ/መገምገም(Evaluating)*
ተማሪዎች የሚያነቧቸው ጽሑፎችና የጽሑፎቹ አይነት የተለያዩ እየሆኑ በሄዱ ቁጥር ያነበቡትን ጽሑፍ ለመመዘን/ለመገምገም የሚኖራቸው ፍላጎትም እያደገ ይመጣል። በአንብቦ መረዳት ዐውድ መገምገም ሲባልም የሚያነቡትን ጽሑፍ ይዘትና ቅርፅ በተመለከተ ፍርድ ወይም ዳኝነት ወይም አስተያየት የመስጠት ችሎታን የሚመለከት ነው። ይህም እውነታዎችንና አስተያየቶችን መለየትን፣የመረጃዎችን አስተማማኝነት መመዘንን ወዘተ. ያካትታል። ግምገማ ፀሐፊው ጽሑፉን ለመጻፍ የሚያበቃው ደረጃ አለው? የፀሐፊው አመለካከት ግላዊነት/አድሎ (bias) የሚንጸባረቅበት ነው? በጽሑፉ ውስጥ ያልተገለጹ ሌላ አይነት አመለካከቶች አሉ?የግል አስተያየቶች በእውነታዎች፣በስታትስቲኮችና በማስረጃዎች የተደገፉ ናቸው? የሚሉ አይነት ጥያቄዎችን እያነሱ የጽሑፉን የተቀባይነት ደረጃ የመፈተሽ ሂደትም ነው (ግሊንከ፣1976)።

## ጥልቅ ንባብና ሰፊ ንባብ (Intensive Reading & Extensive Reading)

በሌላ ክፍል በመጠኑ እንደተወሰው፣ ማንበብ ለሰው ልጅ በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ የሆነ ክሂል ነው (ፔተልና ጀን፣2008)። ይህ ክሂል ከመናገርና ከመጻፍ ክሂሎች ይልቅ በጣም አስፈላጊ ነው። በማንኛውም ቋንቋ ትምህርት ዋነኛውን ቦታ የማንበብ ክሂል ተግባር እንዲይዝ የሚደረገውም ለዚህ ነው (ፔተልና ጀን፣2008)። የማንበብ ክሂል የመረጃና የደስታ ምንጭ ብቻ ሳይሆን የቋንቋ ችሎታ የሚሻሻልበትና የአዕምሮ የማመዛዘን ደረጃ የሚያድግበትም ነው። የሌሎች ሰዎችንና ህዝቦችን ባህልና የህይወት ልምድ መማሪያና ከታላላቅ ሰዎች አዕምሮ ጋር መገናኛም ነው(ፔተልና ጀን፣2008)።

በትምህርት ቤት እንዲዳብሩ የሚጠበቁ ዋነኛ የንባብ አይነቶችም ጥልቅና ሰፊ ንባብ የሚባሉት ናቸው። ጥልቅ ንባብ የሚባለው በአብዛኛው ቀደም ሲል የቀረቡትን አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎች የሚመለከት ነው። ለምሳሌ አንድን አጭር ጽሑፍ መስመር በመስመር በማንበብና በመመርመር የጽሑፉን ዋና ዋናና ጠቃሚ ዝርዝር ሀሳቦች፣ አንድምታዎች፣መልዕክቶች ወዘተ. የመረዳት ሂደት በጥልቅ ንባብ ትምህርት መነሻነት የሚዳብሩ ንዑሳን ክሂሎች ናቸው። በአጥኝው የተደረጉ ቀደምት ንባቦች የሚያሳዩት በመማሪያ መጽሐፎች ውስጥ ብዙ ጊዜ የሚካተቱ ምንባቦች ዋና ዓላማ በጥልቅ ንባብ ሊዳብሩ የሚገባቸው ክሂሎች ላይ የሚያተኩሩ መሆናቸውን ነው። በእነ ሪቻርድስ (2002) ስራ የተጠቀሱት ካሬልና ካርሰን (1997) እንዲሁም ብራውን (2007) እንደገለጹት ለተማሪዎች የወደፊት ህይወት ከሚኖረው አስፈላጊነት አንጻርም በንባብ ትምህርት ስርዓት ሰፊ ንባብም ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

ሰፊ ንባብ ሰፋ ያለን ጽሑፍ (ለምሳሌ መጽሐፍን) በማንበብ ብዙውን ጊዜ የጽሑፉን አጠቃላይ ሀሳብ ለመረዳት የሚካሄድ የንባብ አይነት ነው። ሰፊ ንባብ ከጥልቅ ንባብ የሚለየውም አንደኛ ጥልቅ ንባብ በአጫጭር ጽሑፎች( ቴክስቶች) ላይ በመምህሩ መሪነት የሚከናወን ነው። ሰፊ ንባብ ግን በተማሪው ኃላፊነት በግል የሚከናወን ነው። ሁለተኛ የጥልቅ ንባብ ዋነኛ ዓላማ ስለምንባቡ ጥልቅ ፍቾ ለማግኘትና አንብቦ የመረዳት ክሂሎችን ለምሳሌ ዋና ዋና ሀሳቦችን መለየት፣ በጽሑፉ ውስጥ የቀረቡ ሀሳቦችን የርስበርስ ግንኙነቶች ለመገንዘብ፣እንዲሁም የቃላትና የሰዋስው ዕውቀትን ለማዳበር ነው። በሰፊ ንባብም እነዚህ ክሂሎች የሚዳብሩ ቢሆኑም ዋና ዓላማው ከዚህ የተለየ ነው። ከዚህ በመነሳትም በንባብ ትምህርት ለሁለቱም የንባብ አይነቶች ትኩረት መስጠት እንደሚገባ ሪቻርደሰንና ሬናዲያ (2002)እና ብራውን (2007) የተለያዩ የጥናት ውጤቶችን በማጣቀስ ያስገነዝባሉ፤ፔቴልና ጀን (2008 )ም ይህንኑ ሀሳብ ይጋራሉ። በእርግጥ ላይ ላዩን ሲታዩ እነዚህ ክሂሎች ተቃራኒ ይመስላሉ። ሆኖም ግን በጥልቀት ሲፈተሹ አንዱ የሌላኛውን ጉድለት የሚሞሉ ናቸው።

በሰፊ ንባብ ትምህርት ተማሪዎች ያነበቡትን በቃል ወይም በጽሑፍ ሪፖርት እንዲያደርጉ ማድረግ አንዱ ዘዴ ነው። የሚነበቡ ተመሳሳይ ጽሑፎችን በቡድን አከፋፍሎ እንዲያነቡና ያነበቡትን ሪፖርት እንዲያደርጉ ማድረግም ይቻላል። በአጠቃላይ በሰፊ ንባብ ላይ የሚሰጡ የቤት ስራዎችና "አሳይመንቶች" ተማሪዎች የተለያዩ ጽሑፎችን እንዲያነቡ ያበረታታሉ (ፔቴልና ጀን፣2008)።

የሰፊ ንባብ ባህርያትና ጠቀሜታዎችን በመጠኑም ቢሆን መመልከቱ የተባለውን ሀሳብ ግልጽ ሊያደርገው ይችላል። በፔቴልና ጀን (2008) እና ሬናዲያና ጃኮብስ (2002) ስራዎች መሰረት ሰፊ ንባብ የሚከተሉት መሰረታዊ ባህርያትና ጠቀሜታዎች አሉት፤

የተማሪዎችን የቃላት ችሎታ ያዳብራል፤ድምጽ ሳያሰሙ/ከንፈር ሳያንቀሳቅሱ የማንበብ ልምድን ያዳብራል። በጭብጦች ላይ አተኩሮ ማንበብን ያለማምዳል። ተማሪዎች ሰፋ ያሉ ጽሑፎችን (ማቴሪያሎችን)እንዲያነቡ ዕድል ይፈጥራል። አብዛኛውን ጊዜ ተማሪዎች የሚያነቡትን ጽሑፍ የመምረጥ ዕድል እንዲያገኙ ያደርጋል። በርዕሰ ጉዳይና በጽሑፍ አይነት የተለያዩ ስራዎችን የማንበብ ዕድል ይፈጥራል። ተማሪዎች አንብበው መረዳት በሚችሉት ደረጃ ለማንበብ ያስችላቸዋል። ከንባብ በኋላ በሚከናወኑ ተግባራት በንቃት እንዲሳተፉ ያደርጋል። ዋናውን ሚና ተማሪዎች እንዲጫወቱ ያደርጋል። ጥሩ የንባብ ልምድ ያዳብራል።

ጠቀሜታዎችን በሚመለከት ደግሞ የተማሪዎችን ቋንቋ የመማር ሂደት ያፋጥናል። ስለዓለም የሚኖር ዕውቀትን ይጨምራል። የማንበብና የመጻፍ ክሂሎችን ያሻሽላል። በማንበብ መደሰትን ለማዳበር ያስችላል። ለማንበብ አዎንታዊ አመለካከትን ይፈጥራል። የማንበብ ልምድን በከፍተኛ ደረጃ ያሳድጋል ተብሎ ይታመናል።

ከላይ በዐቢይ ንዑስ ክሂልነት ከቀረቡት የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች መካከል አንደኛ በሀገሪቱ ነባራዊ ሁኔታዎች ሊተገበሩ የሚችሉት ፤ሁለተኛ በክለሳው ክፍል በአንድ ክሂል ስር ከአንድ በላይ ንዑስና የንዑስ ንዑስ ክሂሎች ቢቀርቡም በዚያ መንገድ ባለሙያቹ (መምህራኑ) እንዲዛመዱ ቢደረግ፤ አንደኛ፣የምደባ ሂደቱ ባለሙያዎችን የሚያደክም ሊሆን ይችላል ሁለተኛ፣ ስራውን የተንዛዛ ሊያደርገው ይችላል። በመሆኑም በክለሳው ከቀረቡት የአንብቦ መረዳት ክሂሎች መካከል በውጤት ትንተናው ክፍል የቀረቡት 20 መሰረታዊ የተባሉ ክሂሎች ብቻ ተመርጠው በጥናቱ ተፈትሸዋል። መዳቢዎቹ ከእነዚህ ክሂሎች ውጭ ቢያገኙ ለመመደብ እንዳይቸሩ ደግሞ በሰንጠረዞቹ ሌላ የሚል ክፍል እንዲካተት ተደርጓል።

## **የአጠናን ዘዴ** /Methodology/

የጥናቱ አይነት ገላጭ በተለይም ገምጋሚ ነው። በመግቢያው እንደተገለጸው የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የአጠቃላይ 2ኛ ደረጃ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች በ20 ምንባቦች ላይ ተመስርተው የቀረቡ 425 ጥያቄዎች፣አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎችንና ጥልቅና ሰፊ የንባብ ችሎታዎችን ለማዳበር ያላቸውን የተገቢነት ደረጃ መፈተሽ ነው። ለዚህ ደግሞ የመረጃ ምንጭ ሆነው ያገለገሉት የዘጠነኛና የአስረኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሐፎች ናቸው። በመማሪያ መጽሐፎቹ የቀረቡ የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችን የተገቢነት ደረጃ ለመመርመርም በተለያዩ መጽሐፎችና ጥናቶች በአንብቦ መረዳት ትምህርትነት ሊቀርቡ የሚገባቸው እንደሆኑ ከሚገለጹት መካከል ዋና ዋና የሚባሉት 20 ክሂሎች በመስፈርትነት እንዲያገለግሉ ተደርገዋል። በመጽሐፎቹ የቀረቡት ጥያቄዎች እንዲዳብሩ በሚጠበቁት የቋንቋ ትምህርት ክፍሎች ውክልና ደረጃ ያላቸውን ግንኙነት እንዴት ማጥናት ይቻላል? በዚህ ጥናት ዐውድ በማንበብ ክሂል ጥያቄዎችና እንዲዳብሩ በሚጠበቁት አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎች ተዛምዶን ለማጥናት/ለመገምገም የሚያገለግሉ ሦስት የአጠናን ዘዴዎች እንዳሉ በእነ ኦልደርሰንና ሌሎች (1995፣193) ስራ ተጠቅሰዋል። ከእነዚህ አንደኛው፤በራሱ በአጥኝው የጥያቄዎችን ይዘት ከልየታዎቹ (እንዲዳብሩ ከሚፈለጉ ክሂሎች) ጋር የማወዳደር/የማዛመድ ስልት ነው። ሁለተኛው መምህራን፣ በሙያው የላቀ ችሎታ ያላቸው ምሁራንና የተግባራዊ ስነ ልሳን ሊቃውንት የሚሞሏቸው መጠይቆችና አስተያየታቸውን የሚገልፁባቸው ቃለመጠይቆችን በማዘጋጀት ነው። ሦስተኛው በጥያቄዎችና ክሂሎች ዝምድና ላይ ባለሙያዎች ዳኝነት እንዲሰጡ የትኛው ጥያቄ የትኛውን ክሂል እንደሚያዳብር እንዲገልፁ (experts judgment) ዕድል የሚሰጠውን ስልት መጠቀም ነው። አብዛኛውን ጊዜ አገልግሎት ላይ እየዋለ ያለውና በWeir እና ሌሎች (1990) ስራ ተመራጭ ዘዴ ሆኖ የቀረበው ሦስተኛው ስልት ነው። ስለዚህ በዚህ ጥናት በመማሪያ መጽሐፎቹ አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች/ጥያቄዎች እና በቋንቋ ትምህርት አንዲዳብሩ በሚፈለጉ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች መካከል ያለውን ግንኙነት ለማጥናት ዋነኛ ዘዴ ተደርገው የተመረጡት አንደኛውና ሦስተኛው ስልቶች ናቸው። በዚሁ መሰረት ከተመራማሪው በተጨማሪ ሁለት አማርኛ ቋንቋን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ከ10 ዓመት በላይ ያስተማሩና አማርኛን በማስተማር ሁለተኛ ዲግሪ ያላቸው የቋንቋው መምህራንና አንድ የመጀመሪያ ዲግሪያቸውን በአማርኛ፣2ኛ ዲግሪያቸውን በስርዓት ትምህርትና ማስተማር የሰሩና ከ15 ዓመታት በላይ አማርኛን ያስተማሩ መምህራን በዓላማ ተኮር ንሞና ዘዴ ተመርጠው ፈቃደኛ ሆነው በመገኘታቸው በመማሪያ መጽሐፎቹ የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ለማስተማር የቀረቡ 425 ጥያቄዎችን፣ከተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ የተወሰዱ በቋንቋ ትምህርት እንዲዳብሩ የሚጠበቁ 20 የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎች ጋር እንዲያዛምዱ ተደርገዋል። መምህራኑ ጥያቄዎችን በቸክሊስትነት እንዲገለገሉባቸው ስለተሰጧቸው ክሂሎች በቂ ግንዛቤ እንዲኖራቸውም መመደብ ከመጀመራቸው በፊት ክሂሎችን በሚመለከት የተካሄደውን ክለሳ እንዲያነቡ ዕድሉ ተሰጥቷቸዋል። ምደባው በአጥኝውና በሦስቱ መምህራን ከተካሄደና በአመዳደባቸው ላይ ልዩነት በታየባቸው ምደባዎች ላይ በእነዊየር(1990) ስራ እንደተመከረው ውይይት በማካሄድ ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኋላ በመማሪያ መጽሐፎቹ የቀረቡ 20 ምንባቦች መሰረትነት የወጡ 425 ጥያቄዎች ለጥናቱ ከተለዩት 20 የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ጋር በማዛመድ የተሰበሰቡት መረጃዎች በገላጭ ስታትስቲክስ በተለይም በቁጥርና በመቶኛ ተተንትነዋል። ከዚያም የውጤት ትንተናዎችን በተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ከቀረቡት አተያዮች ጋር በማገናዘብ ጥያቄዎቹ ከክሂሎቹ ጋር ያላቸው ግንኙነት ምን እንደሚመስልና በመማሪያ መጽሐፎቹ የአንብቦ መረዳት ክፍል ጥያቄዎች አዘገጃጀት የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ንዑሳን ክሂሎችን በማስተማር ረገድ ያለው ሚና ምን እንደሚመስል ለመፈተሽ ተሞክሯል።

## የውጤት ትንተናና ማብራሪያ

### የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ውክልና

ከሰንጠረዥ አንድ ማስተዋል እንደሚቻለው በዘጠነኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ከ20ዎቹ ንዑሳን ክሂሎች 12ቱ ከአስሩ ምዕራፎች በአንዱም በአንድም ጥያቄ መወከል አልቻሉም። ሦስቱ ደግሞ በአንዳንድ ጥያቄ ብቻ ተወክለዋል። ከዚህም በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎችን ለማስተማር የሚያስችሉ ከ10 ያላነሱ ምንባቦች ቢኖሩምእንደሚጠበቀው በቅድመ ንባብ፣ በንባብ ጊዜና በድህረ ንባብ ጊዜ ተግባራት/መልመጃዎች ውስጥ ውክልና እንዳላገኙ ለመረዳት ተችሏል። በሌላ በኩል ደግሞ በተራ ቁጥር 6፣3፣15 እና1 የተመለከቱት ክሂሎች በቅደም ተከተል በ61፣በ50፣በ48 እና 47 ጥያቄዎች ተወክለዋል። (See appendix for Table 1, 2 and 3.)

በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በዘጠኝ ምዕራፎች በመቅረብ በሁለተኛነት የሚከተለው ደግሞ “ዝርዝር ሀሳቦችን የመረዳት ክፍል”፣የሚለው ነው። “በአሰሳ ንባብ ዝርዝር ሀሳቦችን/መረጃዎችን መለየት” የሚለው ክሂልም በዘጠነኛ ክፍል በ9፣ በአስረኛ ክፍል በ8 ምዕራፎች ቀርቧል። “የቃላትን ፍች ከዐውድ መፈለግ”የሚለው ደግሞ በሁለቱም ክፍሎች በሰባት ምዕራፎች በመቅረብ የአራተኛነትን ደረጃ ይዟል። በዘይቤያዊ አገላለጽ የቀረቡ ሀሳቦችን የመረዳት ክሂል በዘጠነኛ ክፍል በሦስት ምዕራፍ በመቅረብ አምስተኛ ደረጃ ላይ የሚገኝ ሲሆን በ10ኛ ክፍል እንዲህ ያለ ትምህርት በአንድም ምዕራፍ አልቀረበም።

ከተጠየቅ አንፃር ሲታይ ግን እንዲህ ያለ ጠለቅ ያለ ማለትም በዘይቤ የቀረቡ ሀሳቦችንና መልዕክቶችን የመረዳት ትምህርት ይበልጥ ተጠናክሮ ሊቀርብ ይገባው የነበረው ተማሪዎች በዕድሜና በትምህርት ደረጃ እያደጉ በሄዱ ቁጥር ነበር ማለት ይቻላል። በእርግጥ በዘጠነኛ ክፍልም ቢሆን በሦስት ምዕራፎች ከቀረቡት ዘይቤ ነክ መልመጃዎች አንደኛው እያነበቡ የዘይቤ አይነቶችን እንዲለዩ የሚጠይቅ ነው፤ በዘይቤያዊ አገላለጽ የቀረቡ ሀሳቦችን አንብቦ መረዳትን የሚያለማምድ አይደለም። አንድ ጽሑፍ የተጠቀመባቸውን የዘይቤ አይነቶች መለየትና በዘይቤዎቹ የተገለፁ ሀሳቦችን መረዳት የተለያዩ ችሎታዎችና ጉዳዮች ናቸው። ስለዚህ በዘጠነኛ ክፍልም ቢሆን በዘይቤያዊ አገላለጽ የቀረቡ ሀሳቦችን ከመረዳት ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያላቸው በሁለቱ ምዕራፎች የቀረቡት መልመጃዎች ብቻ ናቸው ማለት ነው። የጽሑፍን አንድምታ መረዳት ደግሞ በዘጠነኛ ክፍል በሁለት ምዕራፍ፣ በሦስት ጥያቄ፣ በ10ኛ ክፍል በአንድ ጥያቄ ብቻ እንዲወከል ተደርጓል። የአንብቦ መረዳት ትምህርት ዋነኛ ጉዳይነት ከሚጠቀሱት አንዱ የሆነው ዋና ዋና ሀሳቦችን የመለየት ክሂል በሁለቱም መጽሐፎች በአንድ አንድ ጥያቄ ብቻ እንደቀረበ ሰንጠረዦቹ ያመለክታሉ። ሰዋስዋዊና ቃላዊ አያያዦችን መለየትን የሚመለከት ትምህርት በዘጠነኛ ክፍል በአንድ ጥያቄ ብቻ ቀርቧል። በራስ አባባል መግለጽ፣ ማሳጠር፣ መተንተንና ማዛመድ ደግሞ እንዲሁ በአንድ አንድ ጥያቄ ብቻ በ10ኛ ክፍል የመማሪያ መጽሐፍ ተወክለዋል። የጽሑፍን መልዕክት መረዳት የሚለውም እንዲሁ በ10ኛ ክፍል ብቻ በሦስት ምዕራፍ፣ በሦስት ጥያቄዎች ብቻ ቀርቧል።

በአጠቃላይ ሰንጠረዥ ሦስት እንደሚያሳየው በጥናቱ ከተካተቱት 21 አንብቦ የመረዳት ክሂሎች 1ኛ. በግርፍ ንባብ (Skimming) የጽሑፍን መንፈስ መለየት፣ 2ኛ. ርዕሰ ጉዳይን መለየት 3ኛ. የደራሲውን ዓላማ መረዳት፣ 4ኛ. የምስሎችን (የካርቱኖችን፣ ሰንጠረዦችን፣ ስዕሎችን…) አንድምታ መረዳት፣ 5ኛ. ማቀናበር፣ 6ኛ.ግምገማ የሚሉት አምስቱ መሰረታዊ የአንብቦ መረዳት ክሂሎች (ኩታ፣2008፤ስቴርስ፣2006፤ሜዘርናማካርቲ፣2005፤ግርሌት፣1996) በሁለቱም መማሪያ መጽሐፎች አልተካተቱም። ከመካከላቸው አንዳቸውም በአንድም ምዕራፍ በአንድም ጥያቄ አልተወከሉም። ከዚህ በተጨማሪ፣ በዘጠነኛ ክፍል አንደኛ በራስ አባባል የመግለጽ ክሂል፣ ሁለተኛ የጽሑፍን መልዕክት መረዳት፣ ሦስተኛ ያነበቡትን ከቀደመ እውቀትና ከሕይወት ልምድ ጋር ማዛመድ የሚሉት ክሂሎች፣በ10ኛ ክፍል ደግሞ ሰዋስዋዊና ቃላዊ አያያዦችን መለየትና ቀደም ብሎ ለሌላ ዓላማ የተገለፀው በዘይቤ የተገለፁ ሀሳቦችን መረዳት የሚሉት ክሂሎች እንዲሁ በየትኛውም ምዕራፍ በአንድም ጥያቄ ያልተወከሉ ናቸው። ይህም የመማሪያ መጽሐፎቹ የአንብቦ መረዳት ክፍል መልመጃዎች በተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ክፍል ከቀረቡት አስተሳሰቦችና መርሆዎች አንፃር ተቃኝተው እንዳልተዘጋጁ ያሳያል።

በተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ክፍል (ለምሳሌ ኩታ፣2008፤ስቴርስ፣2006፤ሜዘርናማካርቲ ፣2005፣ግርሌት፣1996 እና የትምህርት ሚኒስቴር የስርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ 2010ን በመጥቀስ) እንደተገለፀው ተማሪዎች በእነዚህ ክሂሎች ሰፊ ልምምድ እያደረጉ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸውንና

የማሰብ ችሎታቸውን እንዲያዳብሩ ማድረግ ይጠበቅ ነበር። ሆኖም በጥናቱ የተመረመሩት የመማሪያ መጽሐፎች በዚህ ረገድ የተሳካላቸው እንዳልሆኑ የውጤት ትንተናው አመላክቷል።

### ዝቅተኛና ከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂሎች ውክልና

በመማሪያ መጽሐፎቹ የቀረቡት የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ከዝቅተኛና ከፍተኛ ደረጃ ክሂሎች አንፃር ሲታዩ ደግሞ በዝቅተኛ ደረጃ (በቀጥታ ከምንባቡ የሚገኙ ሀሳቦችንና መረጃዎችን መረዳት) ክሂልነት የሚታወቁት ክሂሎች የተሻለ ውክልና እንደያዙ በሰንጠረዥ ሦስት የቀረበው ውጤት በግልጽ ያሳያል። ከዝቅተኛም በጣም ዝቅተኛ ክሂልነት የሚመደቡት አንደኛ በአሰሳ ንባብ ዝርዝር መረጃዎችን መፈለግ፣ ሁለተኛ ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳትና ሦስተኛ የቃላትን ፍች ከዐውድ መረዳት የሚሉት ሦስት ክሂሎች በ315 ጥያቄ(በ89+167+119) ወይም በ74.12% በመወከል የትምህርቱን ሦስት አራተኛ አካባቢ ድርሻ እንደያዙ የውጤት ትንተናው አሳይቷል። በሌላ በኩል ደግሞ በከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂልነት የሚታወቁትና በብዙ ጥያቄዎች ሊወከሉ የሚገባቸው (የስርዓተ ትምህርት ማዕቀፍ 2010፣ስፔርስ፣2006፤ሜዘርና ማካርቲ፣2005፤ግሪሌት፣1996) ክሂሎች ለምሳሌ፡-1ኛ. ያነበቡትን መተርጎም፣አንድምታ (የጽሑፍ፣ የምስል)፣መተንበይ እና ዘይቤያዊ አገላለጾችን መረዳት (6+0+3+76+16) በ101 ጥያቄ (በ24%)፣ 2ኛ. የመተንተን ክሂል በሁለት ጥያቄ (በ0.47%) እና 3ኛ.የማዛመድ ክሂል በአንድ ጥያቄ (በ0.23%) ብቻ ተወክለዋል። ሌሎቹ ደግሞ በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በአንድም ጥያቄ የመወከል ዕድል እንዳላገኙ በሰንጠረዥ ሦስት የቀረበው የውጤት ትንተና ያሳያል።

ይህም የመማሪያ መጽሐፎቹ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አዘገጃጀት በብሉም (1956)፣ ራኒ እና ሌሎች (2004)፣ሙንዘንሜይ እና ሩቢን (2013) የተተቸውን ዝቅተኛ ችሎታ ላይ ያተኮሩ ጥያቄዎችን የማብዛት ኢተገቢነት ግንዛቤ ውስጥ ያላስገባና አሁን ያለውን ለከፍተኛ ደረጃ ክሂሎች ትኩረት የመስጠት አስፈላጊነትን መርህ ወይም አተያይ (ትምህርት ሚኒስቴር 2010፣ ኩታ፣2008) ችላ ያለ እንደሆነ ያሳያል። ያነበቡትን መተርጎም በሚለው ክፍል ያለው ውጤት ከፍ እንዲል ያደረገውም በየምንባቡ መነሻ ላይ የሚገኙት ተመሳሳይ የሆኑ የትንበያ ጥያቄዎች ናቸው። ከ24% ውስጥ 17.88% እንዲህ ባሉ ለማስተማር ሳይሆን ለመጠየቅ አመች በሆኑ የትንበያ ጥያቄዎች የተያዘ ነው።

በእንዲህ ያሉ ዝቅተኛ ችሎታን ወይም ከምንባቡ በቀጥታ በሚመለሱ ጥያቄዎች ከሚሰጥ ትምህርት ሊጠበቅ የሚችለው ውጤትም ተማሪዎች ላቅ ያለ የማሰብ ችሎታና ጠለቅ ያለ አንብቦ የመረዳት ክሂል ሳያዳብሩ ትምህርታቸውን ሊያጠናቅቁ የመቻላቸው ነገር ነው። ከዚህ በመነሳትም በሌሎች ጥናቶች (ለምሳሌ በዮናስ፣1991) የተገለጹት ተማሪዎች የማያነቡ፣ ቢያነቡም፣የሚያነቡትን ከተለያየ አቅጣጫ የማይመረምሩ፣የማይተረጉሙና የማይተቹ፣ከዚያም አልፎ ማንበብ የማይወዱ እንዲሆኑ በማድረግ ረገድ የመማሪያ መጽሐፎቹ መልመጃ አዘገጃጀት አሉታዊ ሚና እየተጫወተ ነው፤ብሎ መደምደም ይቻላል።

### የጥልቅ ንባብና ሰፊ ንባብ ውክልና

ሌላው በጥናቱ የተፈተሸው ጉዳይ በመማሪያ መጽሐፎቹ ጥልቅ(intensive) ንባብና ሰፊ (extensive)ንባብ ምን ያህል ትኩረት ተሰጥቷቸዋል የሚለው ጉዳይ ነው። በተዛማጅ ድርሳናት ክለሳ ክፍል እንደተገለጸው በአፍ መፍቻም ሆነ በ፪ኛ ቋንቋ ትምህርት ጥልቅ ንባብ ብቻ ሳይሆን ሰፊ ንባብም ትኩረት ሊሰጠውና ተማሪዎች የተለያዩ ጽሑፎችን እያነበቡ የሚሰሯቸው መልመጃዎች በቤት ስራነትና በ"አሳይመንት"ነት እየተሰጣቸው ሊለማመዱ ይገባቸዋል። በዚህ ረገድ በጥናቱ በተካሄደው ፍተሻ ማረጋገጥ የተቻለው ግን በእነዚህ መማሪያ መጽሐፎች ሰፊ ንባብን የሚመለከት አንድም መልመጃ/ጥያቄ መቅረብ አለመቻሉን ነው።

## ማጠቃለያና አስተያየት

የጥናቱ ዋና ዓላማ በመማሪያ መጽሐፎቹ ጥያቄዎች የአንብቦ መረዳት ክሂሎችና የጥልቅና ሰፊ ንባብ ውክልና ምን እንደሚመስል መፈተሽ ነበር። ለዚህ ደግሞ የመማሪያ መጽሐፎቹን አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች በጥልቀት ለመመርመር ተሞክሯል። በተደረገው ምርመራም አንደኛ በአንብቦ መረዳት ክሂልነት ከሚታወቁትና በ፪ኛ ደረጃ ትምህርትነት ሊቀርቡ ከሚገባቸው ክሂሎች መካከል በመማሪያ መጽሐፎቹ ተካተው የተገኙት የተወሰኑት ብቻ ሆነው ተገኝተዋል። በመማሪያ መጽሐፎቹ መልመጃዎች ውስጥ መካተት ሲገባቸው ያልተካተቱ ብዙ ጠቃሚ የአንብቦ መረዳት ክሂሎች እንዳሉ

የውጤት ትንተናው በግልጽ አሳይቷል። ከዚህ በተጨማሪ በመጽሐፎቹ የተሸፈኑት አንብቦ የመረዳት ክሂሎች ውክልናም ተጠየቃዊ(ተመጣጣኝ) እንዳልሆነ (በብዙ ጥያቄዎች ሊወከሉ የሚገባቸው በውስን ጥያቄዎች በአንጻሩም በዚህ ደረጃ በውስን/ ጥቂት ጥያቄዎች ሊወከሉ የሚገባቸው በብዙ ጥያቄዎች እንዲወከሉ እንደተደረገ) የውጤት ትንተናው አመላክቷል። ይህም በአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸው ክሂሎች ተገቢ ትኩረት እንዳላገኙ፣በአንጻሩም ዝቅተኛ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገባቸው ክሂሎች ከፍተኛ ሽፋን እንዳገኙ ያሳያል። ለምሳሌ በአሰሳ ንባብ ዝርዝር መረጃዎችን መፈለግና ለደረጃው የሚኖራቸው ጠቀሜታ ዝቅተኛ የሆኑ ለምሳሌ ዝርዝር ሀሳቦችን መለየትን የሚመለከቱት ጥያቄዎች በሁለቱም መጽሐፎች በየምዕራፎቹ በብዙ ጥያቄዎች ከፍተኛ ውክልና እንዲያገኙ ሲደረጉ፣በሌላ በኩል ደግሞ በመስኩ ምሁራንና በሀገሪቱ የትምህርት ፖሊሲና በፖሊሲ ማስፈጸሚያ ሰነዱ በጣም አስፈላጊ ክሂልነት የሚጠቀሱት የየአንቀጾችን (የጽሑፍን) ርዕሰ ጉዳዮች፣ ዋና ዋናና ጠቃሚ ዝርዝር ሀሳቦች (major details)፣ አንቀጾች የተስፋፉባቸውን ዘዴዎች መለየት፣ያነበቡትን መተርጎምና ከቀደመ ንባብና ልምድ ጋር ማዛመድ፣ መተንተን፣ ማቀናበርና መገምገም የሚሉት ደግሞ ዝቀተኛ ትኩረት ተሰጥቷቸዋል ወይም ጭራሹኑ ተዘንግተው ተገኝተዋል። ሁለተኛው የጥናቱ ትኩረት በመማሪያ መጽሐፎቹ ለዝቅተኛና ከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂሎች የተሰጣቸውን ትኩረት መመርመር ነበር። በዚህ ረገድ የተደረገው ፍተሻ እንዳሳየውም በመማሪያ መጽሐፎቹ የተለየ ትኩረት የተሰጠው ለከፍተኛ ደረጃ ክሂሎች ሳይሆን ዝቅተኛ ደረጃ ለሚባሉት ነው። የጥናቱ ሦስተኛው ጥያቄ በመልመጃዎቹ ጥልቅና ሰፊ የሚባሉት የንባብ አይነቶች የተሰጣቸው ትኩረት የተመረመረበት ክፍል ነው። በምርመራው ሰፊ የሚባለው የንባብ አይነት በየትኛውም የመማሪያ መጽሐፍ በአንድም ጥያቄ እንዳልተወከለ ለማረጋገጥ ተችሏል። በአጠቃላይ በሦስቱም ጉዳዮች ላይ የተካሄደው የውጤት ትንተና የመማሪያ መጽሐፎቹ የአንብቦ መረዳት ንዑሳን ክሂሎችን የሚመለከቱ የቅድመ ንባብ፣ የንባብ ጊዜና የድህረ ንባብ ጥያቄዎች አዘገጃጀት በተዛማጅ ድርሳናት የቀረበውን የክሂሎች አቀራራብ መንገድ የሚጻረር እንደሆነ አመላክቷል።

## አስተያየት

የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት የአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች አንብቦ የመረዳት ክሂሎችን በአግባቡ ለማስተማር የማያስችሉ እንደሆኑ ከላይ የቀረቡት የጥናቱ ግኝቶች አመላክተዋል። ከእነዚህ ግኝቶች በመነሳትም ለሚመለከታቸው አካላት የሚከተሉት አስተያየቶች ተሰጥተዋል፤

ሀ. የመማሪያ መጽሐፎችን ዝግጅት በተመለከተ፤

ወደፊት የመማሪያ መጽሐፎቹ ሲሻሻሉ ወይም ሲቀየሩ፤ አንደኛ፣ በ፪ኛ ደረጃ ትምህርትነት ሊካተቱ የሚገባቸው አንብቦ የመረዳት ክሂሎች ሁሉ የሚካተቱበት አሰራር ቢቀየስ፣ ሁለተኛ፣ በንባብ ትምህርት ሊቃውንት ትኩረት ሊሰጣቸው እንደሚገባ ለሚታመንባቸው ለህይወት በጣም ጠቃሚና አስፈላጊ ክሂሎች የተለየ ትኩረት ለመስጠት ጥረት ቢያደርጉ፤ ሦስተኛ፣ ከዝቅተኛዎቹ ይልቅ ለከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂሎች የተለየ ትኩረት/አጽንኦት የሚሰጥበት መንገድ ቢፈለግ። አራተኛ፣ በመልመጃዎቹ ሁለቱም የንባብ አይነቶች (ጥልቅና ሰፊ ንባብ) ትኩረት እንዲያገኙ የሚደረግበት ስልት ቢመቻች።

ለ. የቋንቋው መምህራንን በሚመለከት፤

የአጠቃላይ ፪ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የአማርኛ መምህራን የመማሪያ መጽሐፎቹ ለደረጃው የሚመጥኑ የተለያዩ የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን በአግባቡ ለማስተማር የሚያስችሉ ሆነው መዘጋጀት እስኪችሉ ድረስ ከዝቅተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂሎች ርዕሰ ጉዳይን፣ ዋና ዋናና ጠቃሚ ዋነኛ ዝርዝር ሀሳቦችን (major details)፣የደራሲውን ዓላማና አመለካከት፣አንቀጾች የተስፋፉባቸውን መንገዶች፣ቃላዊና/ሰዋስዋዊ አያያዦችን መለየትንና ከፍተኛ ደረጃ አንብቦ የመረዳት ክሂሎችን ለማዳበር የሚያስችሉ ልዩ ልዩ መልመጃዎችን እያዘጋጁ ቢያስተምሩ የችግሮችን መጠንና ደረጃ ለመቀነስ ይቻላል።

## ዋቢዎች


አማረ ማሞ። 1976። የቀለም ጠብታ። አዲስ አበባ፤የኢትዮጵያ መጻሕፍት ድርጅት።

አገኘሁ ተስፋ። 2005 ። የኢትዮጵያ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ማጠናቀቂያ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና በመምህራን የማስተማር ቅድመ ዝግጅትና የማስተማር ተግባር ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ላይ የቋንቋው መምህራን ያላቸው ግንዛቤ (Perceptions)። በአማርኛ ቋንቋና የባህል ዘርፎች አንደኛው አገር አቀፍ ዐውደ ጥናት መድብል፤ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ።

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር። 2004። አማርኛ የተማሪው

ሰንጠረዥ አንድ፡-በዘጠነኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ውክልና የሚያሳይ

| ምዕራፍ | የክሂሉ አይነት | በየምዕራፉ የተጠየቁ ጥያቄዎች ተራ ቁጥር | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ምዕራፍ 1 | ምዕራፍ 2 | ምዕራፍ3 | ምዕራፍ 4 | ምዕራፍ 5 | ምዕራፍ 6 | ምዕራፍ 7 | ምዕራፍ8 | ምዕራፍ9 | ምዕራፍ 10 | ጠቅላላድ ምር |
| 1 | በአሰሳ ንባብ መረጃ መፈለግ | 0 | ፬ 1-4 | ፪ 1- 5<br>፩ 1:3 | ፬ 1-10 | ፬ 1:4<br>፪ 1:4 | ፬<br>1-4፣ 6:7 | ፬ 1-5<br>፪ 2- 5 | ፬ 6፣ 8 | ፬ 6:7 | ፪ 8-10 | 47 |
| 2 | በግርፍ ንባብ ሀሳብ ማግኘት | | | | | | | | | | | 0 |
| 3 | የቃላትን ፍች ከዐውድ መረዳት | ፫ 1-7 | | ፫ 1-7 | | | ፪ 1-8 | ፫ 1-5 | ፪ ሀ-ሸ | ፫ 1-6 ፍካ፡ ፈሊ. | ፬ 6 ፫ 1-10 | 50 |
| 4 | ርዕሰ ጉዳይ መለየት | | | | | | | | | | | 0 |
| 5 | ዋና ሀሳብን መለየት | | | | | | | | | | ፩ ዋ ለዩ | 1 |
| 6 | ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት | ፬ 1-5<br>፪ 1-7 | ፪ 1-4 | ፬ 1-5 | ፪ 1-4<br>፩ 1-5 | | ፬ 5:8:9<br>፫ 2:3:4 | ፪ 1 | 1:4:5:7:9 | 1-5 | ፬ 1-5፡ 7-10<br>፪ 1:4-7 | 61 |
| 7 | የደራሲውን ዓላማ መረዳት | | | | | | | | | | | 0 |
| 8 | አያያዦች/መሸጋገሪያዎች | | | | | | | | | ፪ | | 1 |
| 9 | አንቀጾች የተስፋፉበትን ዘዴ መለየት | | | | | | | | | | | 0 |
| 10 | በራስ አባባል መግለጽ | | | | | | | | | | | 0 |
| 11 | ማሳጠር | | | | | | | | ፫ ለጽሀ | | | 1 |

Appendix :

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 12 | አንድምታ የጽሑፍ | | | | ፫1 ብቻ | | | | | | ፪ 2፡3 | 3 |
| 13 | አንድምታ የምስሎች | | | | | | | | | | | 0 |
| 14 | አንድምታ መልዕክት | | | | | | | | | | | 0 |
| 15 | አንድምታ ትንበያ | ቅ1-3+1 | ቅ 1-4 | ቅ1-3+1 | ቅ1-4+1 | ቅ1-4+1 | ቅ1-5+1 | ቅ 1-3 | ቅ 1-5 | ቅ1-4 | ቅ1- 5+ 1-3 | 48 |
| 16 | ዘይቤያዊ አገላለጾችን መረዳት | | | | | ፩2፡3፡5 ፪2፡3፡5፡6 ፫ 1-5 | ፪፡፫የዘመ ነኞቱ | ፩2፡3 መለየት | | | | 16 |
| 17 | የመተንተን ክሂል | | | | | | | | | | | 0 |
| 18 | የማዛመድ ችሎታ | | | | | | | | | | | 0 |
| 19 | የማቀናበር ክሂል | | | | | | | | | | | 0 |
| 20 | የመገምገም ክሂል | | | | | | | | | | | 0 |
| 21 | ሌላ ክሂል | | | | | | | | | | | 0 |

በ10ኛ ክፍል ያለው እውነታም ከዘጠነኛው የተለየ እንዳልሆነ በሰንጠረዥ ሁለት የቀረበው የባለሙያዎች የጥያቄ-ክሂል ምደባ በግልጽ ያሳያል። እንደቀዳሚው ሁሉ በዚህኛው መጽሐፍ 10 ክሂሎች በአንድም ጥያቄ ያልተወከሉ ሲሆን አራቱ ደግሞ በአንዳንድ ጥያቄ ብቻ ተወክለዋል። በአንጻሩም በተራ ቁጥር 6፣3፣1 እና 15 የተጠቀሱት ክሂሎች በቅደም ተከተል በ58፣57፣42 እና28 ጥያቄዎች ተወክለዋል። ይህም የክሂሎቹ ውክልና ተመጣጣኝና ተጠየቃዊ/ሎጅካል የሚባል እንዳልሆነ ያመላክታል።

ሰንጠረዥ ሁለት:- በአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ መልመጃዎች የአንብቦ መረዳት ክሂሎችን ውክልና የሚያሳይ

| ምዕራፍ | የክሂሉ አይነት | በየምዕራፍ የተጠየቁ ጥያቄዎች ተራ ቁጥር | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ምዕራፍ1 | ምዕራፍ 2 | ምዕራፍ3 | ምዕራፍ 4 | ምዕራፍ 5 | ምዕራፍ 6 | ምዕራፍ 7 | ምዕራፍ8 | ምዕራፍ9 | ምዕራፍ10 | ጠቅላላ ድምር |
| 1 | በአሰሳ ንባብ መረጃ መፈለግ | ፩1-5<br>፪ 2-5 | ፩ 1-5 | ፫1፣2 | ፩ 1-5 | ፩ 1- 5 | ፩ 4፣5<br>፪1-5 | | | ፪ 2-4 | ፩ 1-5<br>፫ ሀ | 42 |
| 2 | በግርፍ ንባብ ሀሳብ ማግኘት | | | | | | | | | | | 0 |
| 3 | የቃላትን ፍች ከዐውድ መረዳት | | ፫ ሀ- ሠ<br>፬ ሀ-ሠ | ፪ 1-5 | ፪ 1-5<br>፫ 1-5 | | | ፪ ሀ-ረ | ፪ 1-8 | ፪ 1<br>፫1-6 ፬1-6 | ፪ ሀ-ሠ | 57 |
| 4 | ርዕሰ ጉዳይን መለየት | | | | | | | | | | | 0 |
| 5 | ዋና ሀሳብን መለየት | | | | | | | | | | ፬ ዋ ለጸ | 1 |
| 6 | ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት | ፩ 1-5<br>፪ 1-7 | ፪ 1-4 | ፩ 1-5 | ፪ 1-4<br>፬ 1-5 | | ፩ 5፣8፣9<br>፫ 2፣3፣4 | ፪ 1 | 1፣4፣5፣7፣9 | 1-5 | ፩1-5፣7-10<br>፪ 1፣4-7 | 58 |
| 7 | የደራሲውን ዓላማ መረዳት | | | | | | | | | | | 0 |
| 8 | አያያዦችን/መሸጋገሪያዎችን መለየት | | | | | | | | | | | 0 |
| 9 | የአንቀጽ ማስፋፊያዎችን መለየት | | | | | | | | | | | 0 |
| 10 | በራስ አባባል መግለጽ | | | | | | | | | | ውስጠ | 1 |

| | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 11 | ማሳጠር | | | ሐ ውስጠ | | | | | | | | 1 |
| 12 | አንድምታ_ የጽሑፍ | | | | | | | | | | ፭ ለ-መ | 3 |
| 13 | አንድምታ_ የምስሎች | | | | | | | | | | | 0 |
| 14 | አንድምታ_ መልዕክት | | | | | | | | ፫ 5 | ፰ 5 | ፫ ሠ | 3 |
| 15 | አንድምታ_ ትንበያ | ቅ1 | ቅ 1-3 | ቅ ለ | ቅ1-3 | ቅ1-4+1 | ቅ1-3 | ቅ 1-2 | ቅ 1-4 | ቅ1-4 | ቅ1- 2 | 28 |
| 16 | ዘይቤያዊ አገላለጾችን መረዳት | | | | | | | | | | | 0 |
| 17 | የመተንተን ክሂል | | | | | ፫ 2፡3 | | | | | | 2 |
| 18 | የማዛመድ ችሎታ | | | | | ፫ 1 | | | | | | 1 |
| 19 | የማቀናበር ክሂል | | | | | | | | | | | 0 |
| 20 | የመገምገም ክሂል | | | | | | | | | | | 0 |
| 21 | ሌላ ክሂል | | | | | | | | | | | 0 |

በሰንጠረዥ አንድና ሁለት ከቀረቡት መረጃዎች ማስተዋል እንደሚቻለው በዘጠነኛም ሆነ በአስረኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች በተለያዩ ምዕራፎች የተሻለ ውክልና ካገኙት አንብቦ የመረዳት ክሂሎች መካከል አንደኛው የትንበያ ክሂል ነው። የመተንበይ ክሂል በተደጋጋሚ የተከሰተው በቅድመ ንባብ ተግባርነት ቢሆንም በሁለቱም የክፍል ደረጃዎች በሁሉም ምዕራፎች የመሸፈን ዕድል አግኝቷል።

ሰንጠረዥ ሦስት፡- የአንብቦ መረዳት ክሂሎች ውክልና በ9ኛና በ10ኛ ክፍል የአማርኛ መማሪያ መጽሐፎች መልመጃዎች

| የመጽሐፎቹ ምዕራፍ | የክሂሉ አይነት | በ9ኛና 10ኛ ክፍል በየክሂሉ የተጠየቁ ጥያቄዎች ድምርና ጠቅላላ ድምር | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | የ9ኛ ክፍል ድምር | | የ10ኛ ክፍል ድምር | | ጠቅላላ ድምር | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛት | % |
| 1 | በአሰሳ ንባብ መረጃ መፈለግ | 47 | 20.6 | 42 | 21.3 | 89 | 20.9 |
| 2 | በግርፍ ንባብ ሀሳብ ማግኘት | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| 3 | የቃላትን ፍች ከዐውድ መረዳት | 50 | 21.9 | 57 | 28.9 | 107 | 25.2 |
| 4 | ርዕሰ ጉዳይ | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| 5 | ዋና ሀሳብን መለየት | 1 | 0.4 | 1 | 0.5 | 2 | 0.5 |
| 6 | ዝርዝር ሀሳቦችን መረዳት | 61 | 26.8 | 58 | 29.4 | 119 | 28.0 |
| 7 | የደራሲውን ዓላማ መረዳት | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| 8 | አያያዦች/መሸጋገሪያዎች | 1 | 0.4 | 0 | 0 | 1 | 0.2 |
| 9 | አንቀጾች የተስፋፉበትን ዘዴ መለየት | | | | | 0 | |
| 10 | በራስ አባባል መግለጽ | 0 | 0 | 1 | 0.5 | 1 | 0.2 |
| 11 | ማሳጠር | 1 | 0.4 | 1 | 0.5 | 2 | 0.5 |
| 12 | እንድምታ_ የጽሑፍ | 3 | 1.3 | 3 | 1.5 | 6 | 1.4 |
| 13 | እንድምታ_ የምስሎች | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| 14 | እንድምታ_ መልዕክት | 0 | 0 | 3 | 1.5 | 3 | 0.8 |
| 15 | እንድምታ_ ትንበያ | 48 | 21.1 | 28 | 14.2 | 76 | 17.93 |
| 16 | ዘይቤያዊ አገላለጾችን መረዳት | 16 | 7.0 | 0 | 0 | 16 | 3.8 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 17 | የመተንተን ክሂል | 0 | 0 | 2 | 1.0 | 2 | 0.5 |
| 18 | የማዛመድ ችሎታ | 0 | 0 | 1 | 0.5 | 1 | 0.2 |
| 19 | የማቀናበር ክሂል | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| 20 | የመገምገም ክሂል | 0 | 0 | 0 | 0 | 0 | |
| 21 | ሌላ ክሂል | | | | | 0 | |
| | ጠቅላላ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ብዛት | 228 | 100 | 197 | 100 | 425 | 100 |